# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 280 ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡ ሀዱሽ አብርሃ

# ኢድ አል አድሃ የአብሮነት፣ የመተሳሰብና የትብብር በዓል ነው

## - 1445ኛው የአረፋ በዓል በድምቀት ተከብሯል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- 1445ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ በዓል) የአብሮነት፣ የመተሳሰብና የትብብር በዓል መሆኑን የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ገለጸ። በዓሉ ትናንት በተለያዩ ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች በአዲስ አበባ ስታዲየም በድምቀት ተከብሯል።

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት የሕዝብ ጉዳዮች ተጠሪ ሀሰን አሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአረፋ በዓል ኢትዮጵያዊ የመረዳዳት ባህልን በእጅጉ የሚያጎለብት ነው።

በእስልምና ከተደነገጉ ሁለት ትልልቅ አስተምህሮቶች ውስጥ አንዱ ነው ያሉት ሀሰን አሊ፤ አረፋ የእርድ በዓል በመባል ይታወቃል ብለዋል።

አቅሙ የቻለ በዓመት አንድ ጊዜ ሀጅ ሥነ ሥርዓት ለማክበር ወደ ሳውዲ አረቢያ አረፋ መካ ተራራ በመሄድ በዓሉን እንደሚያከብር

ኢድ አል አድሃ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












ማንደፍሮ ንጉሤ (ዶ/ር)

# ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን አርሶ አደሮች ኩታ ገጠም ግብርናን እየተገበሩ ነው

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚሆኑ አርሶ አደሮች ማሳቸውን በኩታ ገጠም እያለሙ መሆኑን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ገለጸ።

ስምንት ነጥብ ስድስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ዩኒቨርሲቲው ለአፍሪካ ሀገራት አየር መንገዶች ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት እየሠራ ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካ ሀገራት አየር መንገዶች ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት እየተሰራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ የሙያ መስኮች ያሰለጠናቸውን 787 ተማሪዎች አስመርቋል።

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የኦፕሬሽን ዘርፍ ዋና ሥራ ስራ አስፈጻሚ ረታ መላኩ እንደገለጹት፤ አየር መንገዱ በአቪዬሽን ዩኒቨርሲቲው በርካታ ቁጥር ያላቸውን የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዜጎች በማሰልጠን ወደ ገበያው እያስገባ ነው።

አየር መንገዱ የአቪዬሽን ዩኒቨርሲቲውን በማጠናከር

ዩኒቨርሲቲው ለአፍሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ረታ መላኩ



ካሴ ይማም

## ኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍን ለኃይል አማራጭነት ለመጠቀም እየሠራች ነው

ገጽ 4



# በክልሉ ከ10 ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት በሰብል ዘር ለመሸፈን እየተሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ቦረና፡- በኦሮሚያ ክልል በመኸር እርሻ ከ10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በሰብል ዘር ለመሸፈን ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። እስካሁን ሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል ዘር መሸፈኑ ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በምሥራቅ ቦረና ዞን በመገኘት የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በመኸር እርሻ 10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል ዘር ለመሸፈን ታቅዷል።




አቶ ጌቱ ገመቹ

አጠቃላይ በመኸር ወቅት በሰብል ዘር ከሚሸፈነው መሬት ውስጥ ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የሚሆነው በክላስተር የሚዘራ ነው ያሉት አቶ ጌቱ፤ እስካሁን ዘጠኝ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማረስ ተችሏል ብለዋል።

በክልሉ ያለውን አቅም አሟጦ ለመጠቀም ቀድሞ ለግብርና የሚያስፈልግ ግብዓት ማሟላት ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራቱንም ነው አቶ ጌቱ የጠቆሙት።

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በተለይ በቆላማና በድርቅ ሲጎዱ የነበሩ አካባቢዎች ላይ በተለየ ሁኔታ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል።

በክልሉ የተሻለ የዝናብ ስርጭት አለ ያሉት አቶ ጌቱ፤ በክልሉ በበልግ እርሻ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል ዘር መሸፈኑን ጠቅሰው፤ ለመኸር እርሻ ውጤታማነትም በቂ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

ከዚህም 28 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል ያሉት አቶ ጌቱ፤ የዘንድሮ ዝናብ ቀደም ብሎ መጀመሩ የበልግ እርሻ ከታቀደው በላይ እንዲሳካ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል።

የምሥራቅ ቦረና ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መስቀሉ ቱሉ በበኩላቸው፤ በዞኑ በበልግ እርሻ ከ141 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በዘር መሸፈኑን ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት ቦረና የሚታወቀው በእንስሳት እርባታ ነው ያሉት አቶ መስቀሉ፤ አሁን ሙሉ የተጠናከረ እርሻ እየታረሰ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



# በክልሉ 400 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ጋምቤላ፡- በጋምቤላ ክልል ከ400 በላይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ መሆናቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

የጋምቤላ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሎው ኡቡፐ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ውስጥ ሰፊ ኢንቨስትመንት እየተከናወነ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በጋምቤላ ክልል ከ400 በላይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ ናቸው።በእነዚህ ፕሮጀክቶች ከአንድ ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ በክልሉ ለግብርና ኢንቨስትመንት ተስማሚ የሆነ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ንብረት አለ።ይህ ለአልሚዎች ጥሩ ዕድልና አማራጭ የሚሰጥ በመሆኑ የበርካቶችን ፍላጎት እያሳዩ ነው።

በክልሉ ሰፊ የእርሻ መሬት መኖሩን የጠቆሙት ኮሚሽነሩ፤ ከ800 ሺህ ሄክታር በላይ የሚሆነው መሬት በእርሻ የሚለማ መሬት መሆኑን አስረድተዋል።በመስኖ ሊለማ የሚችለው መሬትም በጣም ሰፊ መሆኑን ገልጸዋል።

በግብርናና ኢንቨስትመንት በተለይም በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሩዝ፣ ማሾ፣ ወዘተ የሚመረት መሆኑን ጠቅሰው፤ በደጋማው አካባቢ የገበያ ምርቶች ቡና፣ ማር፣ ሻይ ቅጠል፣ ቅመማ ቅመም በሰፊው ኢንቨስት የሚደረግበት ዕድል መኖሩን አስገንዝበዋል፡፡

በእንስሳት ሀብት፣ ዓሳ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት አማራጮችም በክልሉ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑንም አስረድተዋል።

በማዕድን ዘርፍም ዲማ ወረዳ እና ሌሎች አካባቢዎችን ጨምሮ ከፍተኛ አቅም ያላቸው የውጭ ሀገር አልሚዎች ወደ ሥራ መግባታቸውንና ለሀገርም ትልቅ ትርጉም ያላቸው ሥራዎች እየተከናወኑ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሎው ገለጻ፤ ከለውጡ በፊት በክልሉ ከ200 በላይ ባለሀብቶች የነበሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ብድር ወስደው ለሌላ ዓላማ የመጠቀምና ለክልሉም ብሎም ለፌዴራል መንግሥት አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ገብተው ነበር።

በተለይም ሰፋፊ እርሻ ቦታ በመያዝና ከልማት ባንክ በመበደር ለተፈለገው ዓላማ ሳያውሉ በመቅረታቸው ኢንቨስትመንቶቹ ለመልካም አስተዳደር እጦት መንስዔ ሆነው እንደነበርም አስታውሰዋል።

ሆኖም በአሁኑ ወቅት የክልሉ መንግሥትም ሆነ የፌዴራል መንግሥት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹን ሕጋዊ አሠራር በማስያዛቸው ጤናማ አሠራሮች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በመሆኑም 109 ባለሀብቶች በክልሉ በአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ኢንቨስትመንት ውስጥ እየተሳተፉ ነው ብለዋል።

# በግንቦት ወር ከቡና የወጪ ንግድ ከ209 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በግንቦት ወር 43 ሺህ 481 ቶን በላይ ቡና በመላክ 209 ነጥብ 54 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የቡናና ሻይ ባለስልጣን ገለጸ።

የቡናና ሻይ ባለስልጣን የሕዝብ ግንኙነትና የኮሚዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሳህለማርያም ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት በግንቦት ወር ብቻ 43 ሺህ 481 ቶን ቡና በመላክ 209 ነጥብ 54 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል።

በበጀት ዓመቱ 11 ወራት ውስጥም በአጠቃላይ 252 ሺህ 466 ነጥብ 98 ቶን የቡና ምርት በመላክ አንድ ቢሊዮን 208 ሚሊዮን 73 ሺህ ዶላር ተገኝቷል።

ይህ ውጤት ካለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ወቅት ወደ ውጭ ከተላከው ምርት እጅግ ከፍተኛ ውጤት የታየበት ነውም ብለዋል።ለውጤቱ መገኘት መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የጎላ ድርሻ ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ቡናን ከሚያለማው አርሶ አደር ጀምሮ ቡና አቅራቢና ላኪዎች እንዲሁም በአጠቃላይ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ባለሥልጣኑ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር እንዲሁም በግብይት ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በዚህም በተለይም ከግብይት ጋር በተያያዘ በዘርፉ ይስተዋሉ የነበሩ ውስብስብ አሠራሮችን በማስወገድ የተሻለ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋት ተጨባጭ ለውጦች ተመዝግበዋል ሲሉ ጠቅሰዋል።

የገበያ አማራጮቹን ማስፋት በመቻሉም በግብይት ሥርዓት ውስጥ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎች መሠራታቸውን አብራርተዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት ሀገሪቷ ወደ ውጭ ገበያ ከምትልከው ቡና ከ80 እስከ 90 በመቶ ያህሉ አቅራቢውና ላኪው ተስማምተው በሚረካከቡት የግብይት ሥርዓት ነው።በ2013 ዓ.ም በተጀመረው ይህ የቀጥታ ትስስር የግብይት ሥርዓት ወደ ውጭ ገበያ የሚላከው የቡና መጠንና የሚገኘው የገቢ መጠን እንዲሁም የጥራት ደረጃው ከፍ እንዲል አድርጓል።

በዚህም ኢትዮጵያ ከውጭ ምንዛሬ የምታገኘው ገቢ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ቢሊዮን ለመሻገር በቅቷል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

የገበያ ተደራሽነት ከማስፋት አንጻርም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ነባር ገበያዎችን የማቆየት እንዲሁም አዳዲስ የመፍጠር ስትራቴጂዎችን እየተከተለ እንደሚገኝ ተናግረው፤ በዚህም ቀደም ሲል በሀገሪቱ ከአስሩ ቀዳሚ ገዢ ዝርዝር ውስጥ ያልነበሩት እንደ ቻይና፣ ዩናይትድ አረብ ኢምሬትስ፣ ታይዋን፣ ጃፓን እና ሱዳንን የመሳሰሉ ሀገሮችን በአዳዲስ የገበያ መዳረሻነት ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

ነባሮቹን በማቆየት ሥራም የኢትዮጵያ ቡና በዓለም እንዲታወቅ ለማድረግ ዓለም አቀፍ ኢግዚቢሽኖችን በማካሄድና በመሳተፍ። እንዲሁም የቡና ጣእም ውድድር በማካሄድ መዳረሻዎችን ለማስፋት፣ እየተሠራ እንደሚገኝ ነው የተናገሩት።

ይህን አበረታች ውጤት ለማስቀጠልም የዋና ዋና ላኪዎችን አፈጻጸም የመገምገምና የማበረታታት፤ አዳዲስ ኮንትራቶችን እንዲገዙ የማድረግ እንዲሁም ሌሎች ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ይገኛል።በተጨማሪ የወጪ ንግድ ግኝቱን የበለጠ ለማሳደግ ክልሎችን ጨምሮ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል ብለዋል።

# በትግራይ ክልል አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በአዝርዕት ለመሸፈን እየተሠራ ነው

## • ከአራት መቶ ሺህ ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሉ ገብቷል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በአዝርዕት ለመሸፈን እየተሠራ መሆኑን የክልሉ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ አስታወቀ። ከአራት መቶ ሺህ ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሉ ገብቷል፡፡

የቢሮው ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሚኪኤለ ምሩፅ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ዘንድሮ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬትን የተለያዩ አዝርእት በመሸፈን ሃያ አራት ሚሊዮን ኩንታል ገደማ ምርት ለመሰብሰብ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

እርሻው ውጤታማ እንዲሆን የተለያዩ ግብአቶች ያስፈልጉታል ያሉት ኃላፊው፤ ከእነዚህ መካከል የስልጠና ዝግጅት አንዱ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኅብረተሰቡ በተለይ ገበሬው ላለፉት ሦስት ዓመታት ከመደበኛ ሥራው ርቆ በመቆየቱ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ አስፈላጊውን የእርሻ ሥራ እና የእንስሳት ሀብት ለማዳበር ስልጠና እየሰጠን ነው ብለዋል፡፡

ከአራት መቶ ሺህ ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ወደ ክልሉ መግባቱን የገለጹት ኃላፊው፤ መንግሥት አቅርቦቱን በወቅቱ በማስገባቱ ምሥጋና አቅርበዋል፡፡



**አቶ ሚኪኤለ ምሩፅ**

ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ኩንታል ገደማ የአፈር ማዳበሪያ ወደ ወረዳዎች መሰራጨቱን ጠቅሰው፤ አጠቃላይ ክልሉ የሚያስፈልገው የማዳበሪያ አቅርቦት ሰባት መቶ ሺህ ኩንታል እንደሆነ እና ቀሪው በሂደት ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

የማዳበሪያ ዋጋ ውድ የሚባል ባይሆንም ገበሬው ከገቢ አንፃር ተዳክሞ በመቆየቱ ይቸግረዋል ያሉት አቶ ሚኪኤለ፤ የአዝርእት እጥረት መኖሩንም ጠቅሰዋል።በተለይ በሦስቱም የአፋር አዋሳኝ ዞኖች ላይ የድርቅ ክስተት ስለነበረ የሚዘራው ዘር አይኖረውም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ በሰሜን ምዕራብ እና በማዕከላዊ ዞን ላይ ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያት የሰብል ዘር የለም፤ በመሆኑም ይህን ችግር ለመፍታት ከተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እና ባለ ድርሻ አካላት ጋር እየሠራን ነው ብለዋል።በዚህም ሰባት ሺህ ገደማ ምርጥ ዘር አሰባስበናል ብለዋል፡፡

በክልሉ በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው የርጥበት ስርጭት ችግር ለመቅረፍ ገበሬው ሰፊ ርጥበት የመሰብሰብ ሥራዎች እንዲሠራ ለማድረግ የውሃ እና ኢነርጂ ቢሮ የሚመራው ግብረ ኃይል መቋቋሙን በመጥቀስ፤ ከባለ ሀብቶች ጋር በመተባበር የቴሌቶን ሥራዎች በመሥራት በአፅቢ ወንበርታ እና በራያ አካባቢዎች ሰፊ የርጥበት ማቆሪያ ስፍራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከዝናብ ጋር ተያይዞ የተገኘውን የውሃ ርጥበት በመሰብሰብ የመስኖ ሥራ እንዲያጠናክር እና አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ባልተገባ መንገድ የአፈር ማዳበሪያ የሚሸጡ ነጋዴዎች ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ አሳስበዋል፡፡

# “የሀገር ሽማግሌዎች በሀገራዊ ምክክሩ ተገቢውን ሚና ሊወጡ ይገባል”

## - የቀብሪደሃር ከተማ ኡጋዞች

**ኢያሱ መሰለ**

ቀብሪደሃር፡- የተጀመረው ሀገራዊ ምክክር ውጤት እንዲያስገኝ በመላ ሀገሪቱ ያሉ የሀገር ሽማግሌዎች ሚናቸውን እንዲወጡ የቀብሪደሃር ከተማ ኡጋዞች ጥሪ አቀረቡ።

የቀብሪደሃር ከተማ ነዋሪ ኡጋዝ መሐመድ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክሩ ውጤት እንዲያስገኝ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል። እንደ ኡጋዝ መሐመድ፤ በአንዳንድ ክልሎች እየተከሰተ ያለው የሰላም ችግር የእኛም የጋራ ችግር ነው።መሣሪያ ታጥቀው የሚታገሉ አካላትም ሆኑ መንግሥት ችግሮችን በንግግር እንዲፈቱ እንመክራለን ብለዋል።

ሕዝብ ለመከራ መዳረግ ስለሌለበት ተመካክሮ ስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልጋል ያሉት ኡጋዝ መሐመድ፤ ለዚህ እንዲበጅ ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን በያሉበት ያሉ የሀገር ሽማግሌዎችም ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

መንግሥትም ስለሰላም ሲል ሆደ ሰፊ ሆኖ የውይይት መድረኮችን እያዘጋጀ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያደርገውን ጥረት መቀጠል አለበት ሲሉ ጠቁመዋል።

የሶማሌ ክልል የዘመናት የመልማት ጥያቄዎች እንደነበሩበት ለአብነት የጠቀሱት ኡጋዝ መሐመድ፤ በአካባቢው ታጥቀው ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር ሰላማዊ ንግግር በመደረጉና በሂደቱም ኡጋዞችና ሽማግሌዎች ሚናቸውን በመወጣታቸው በክልሉ ሰላምን ማስፈን ተችሏል ሲሉ አብራርተዋል።

ሌላው የከተማዋ ነዋሪ ኡጋዝ አብዲአማን ዑመር በበኩላቸው፤ ከለውጡ በፊት በአካባቢው የሰላም ችግር በመኖሩ ምክንያት የልማት ጥያቄ አይታሰብም ነበር። ከተማው የወታደር ካምፕ የበዛበት፣ የጦርነት ወሬ የሚሰማበት፣ ሁሌም በስጋት የሚኖርበት፣ ነዋሪዎች ከታጠቁ ኃይሎች ጋር ትተባበራላችሁ ተብለው ወደ





ፎቶ: ገበቦ ገብሬ

**ኡጋዝ መሐመድ ሀሰን**

**ኡጋዝ አብዲአማን ዑመር**

ጦር ካምፕ እየተወሰዱ የሚታሠሩበት፣ የሚገረፉበት ነበር ብለዋል። ከለውጡ በኋላ በአካባቢው ታጥቀው ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር በተደረገው ውይይት የጦርነት ድምጽ ጠፍቶ ክልሉ ሰላም ሆኗል ያሉት ኡጋዝ አብዲአማን፤ የጦር ካምፖች ወደ ፓርክነት መቀየራቸውን ተናግረዋል።ይህም በሰላም ምክንያት የተገኘ ለውጥ መሆኑን በመግለጽ፤ የሀገር ሽማግሌዎችና የኡጋዞች ሚናም ቀላል ባለመሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ከሰላም ጋር የሚወዳደር ምንም ነገር አይኖርም ብለዋል። የሶማሌ ክልል ሕዝብ ያገኘውን ሰላም ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍልም እንዲያገኝ እንደሚመኙ ተናግረዋል። ይሄ በትምህርት ፣ በመንገድ ፣ በጤና ዘርፍ ያየነው ለውጥ የተገኘው ሰላም ስለመጣ በመሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ሰላምን ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ማገዝ እንደሚኖርባቸው ነው የገለጹት።



**አቶ ኡስማን ሱሩር**

# ተፋሰሶችን

## በፍትሐዊነትለመጠቀም የጋራ ዕቅድ ያስፈልጋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ተፋሰሶችን በፍትሐዊነት ለመጠቀም የጋራ ዕቅድ እንደሚያስፈልግ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተለያዩ ተፋሰሶችን ለልማት በፍትሐዊነት ለመጠቀም የጋራ ዕቅድ ያስፈልጋል፡፡

የክልሉ የውሃ አጠቃቀም ባህልና ፍላጎት በመጨመሩ ግጭት እየተፈጠረ ይገኛል ያሉት አቶ ኡስማን፤ ጉራጌን፣ ስልጤን፣ ሀላባንና ሀዲያን አቋርጦ ኦሮሚያ፣ ሲዳማና ደቡብ ኢትዮጵያን ለሚያዋስነው የዌራ ዲጀ ተፋሰስ ለአብነት አንስተው አስረድተዋል፡፡

ተፋሰሱ የጋራ እቅድ ወጥቶለት በአግባቡ ባለመልማቱና ባለመጠበቁ በላይኛውና በታችኛው ተፋሰስ አካባቢዎች ግጭት እያስነሳ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በውሃ ሀብት ላይ እየተፈጠረ ያለውን ግጭት ሕጋዊ በሆነ አሠራር በመፍታት ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ውሃን በፍትሐዊነት መጠቀምና በዘላቂነት ማልማት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እየተሠራ ነው ብለዋል።ተፋሰስ አስተዳደርና ወሰን አይገድበውም ያሉት አቶ ኡስማን፤ ውሃውን በጋራ በመጠበቅና በማልማት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማዋል በመሠራት ላይ መሆኑን አስረድተዋል።በተፋሰስ ላይ የሚያጋጥሙ ተመሳሳይ ግጭቶችን ለመፍታት የጋራ እቅድ እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል፡፡

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፣ ለተፋሰሶች የጋራ እቅድ ማውጣት ከተቻለ ለማልማት፣ ለማስተዳደር እና ሕግ ለማውጣት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።በዚህም ከክልሎች ጋር ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር ማጠናከር ይቻላል፡፡

በተለያዩ አዋሳኝ አካባቢዎች የሚገኙና የኅብረተሰቡ የመልማት ፍላጎት ከፍ ባለባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ተፋሰሶችን የጋራ እቅድ አውጥቶ በቅንጅት መስራት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።አሠራሩ በውሃ ሀብት ላይ የሚነሳውን ግጭት ለማስቀረት ከመርዳቱም በላይ በዘላቂነት ለማልማት ዕድል ይፈጥራል ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ተፋሰሶችን በዚህ በጋራ ዕቅድ አውጥቶ በቅንጅት መሥራት ተፋሰሶችን ለመጠበቅና በፍትሐዊነት ለመጠቀም እድል ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የኦሞ ጊቤ ተፋሰስ ከሚሸፍነው 79 ሺህ ስኩየር ኪሎ ሜትር 11 በመቶ የሚሆነውን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሚሸፍን መሆኑን ለአብነት ያነሱት አቶ ኡስማን፤ ለኦሞ ጊቤ ተፋሰስ የጸደቀው የተቀናጀ የውሃ ሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር እቅድ የውሃ ሀብቱን በሚፈለገው ደረጃ አልምቶ ለመጠቀም እንደሚረዳ አስረድተዋል፡፡

ውሃን በአግባቡ በማልማትና በመጠቀም የሀገሪቱን እድገት ለማፋጠን የኦሞ ጊቤ ስትራቴጂክ እቅድን ተግባራዊ ለማድረግ እና ግጭቶችን በመፍታት በፍትሐዊነት ለመጠቀም ክልሉ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ አስገንዝበዋል፡፡

ዜና



አቶ ሚሊዮን ማትዮስ

# ኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍን ለኃይል አማራጭነት ለመጠቀም እየሠራች ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በሀገሪቱ የሚገኙ ዋና ዋና ማዕድናትን ለኃይል አማራጭነት በማዋል የካርበን ልቀትን ለመቀነስ እየሰራች ነው ሲል የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማትዮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍን ለኃይል አማራጭነት በመጠቀም የካርበን ልቀትን ለመቀነስ እየሰራች ትገኛለች።

ኮፐር፣ ኒኬል፣ ኮባልት፣ ሊቲየም እንዲሁም ሌሎች ውድና ለኃይል አማራጭ የሚሆኑ የማዕድን ዓይነቶች በኢትዮጵያ የሚገኙ ስለመሆኑ በተለያዩ መንገዶች መረጋገጡን ያመላከቱት አቶ ሚሊዮን፤ ይህም ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ የደረሰውን የካርበን ልቀት ለመቀነስ ትልቁን ድርሻ እንድትወስድ ያስችላታል ሲሉ ገልጸዋል።

በአፍሪካ የሚገኙ ማዕድናት ለኃይል አማራጭ መጠቀም ትኩረት እየሳበ ነው። ይህም የካርበን ልቀትን ከመቀነስ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ነው ያሉት አቶ ሚሊዮን።

በተጨማሪም በኢኮኖሚው ረገድ የማዕድን ዘርፍ በቀጣይ የሀገሪቱን ልማት ከሚወስኑ ዘርፎች መካከል አንዱ እንዲሆን ያስችለዋል ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ሚሊዮን ገለጻ፤ በተለይ ኢትዮጵያ ከካርበን ልቀት ከሚያጋልጡ የልማት ሥራዎች በመላቀቅ አረንጓዴ ኢንዱስትሪ ውስጥ መግባቷ በቀጣይ ለሚኖሩ ተግባራት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥረው ነው። ለአንድ ሀገር ልማት ኃይል ወሳኝ በመሆኑ የተለያዩ ማዕድናትን ማልማት አስፈላጊ ነው።

የማዕድን ልማት አቅጣጫው የካርበን ልቀት መቀነስ ላይ መሠረት ያደረገ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በዘርፉ ያሉ ጸጋዎችን በዘላቂነት መጠቀም ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር መሆኑን አብራርተዋል።

ከማዕድን ልማቱ ጎን ለጎን የተፈጥሮ ጋዝ እና የጂኦ- ተርማል ኃይልን ለተለያዩ ኃይል አማራጮች ለማልማት መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር እየሰራ ይገኛልም ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ ይህን መሰል የልማት አቅጣጫ መከተል ከጀመረች ሦስት ዓመት አስቆጥራለች ያሉ ሲሆን፤ የሚፈለጉት ማዕድናት በኢትዮጵያ የሚገኙ በመሆናቸው በዚሁ ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ከፍተኛ እድል መኖሩን አስረድተዋል።

አቶ ሚሊዮን እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ በማዕድን ልማት ላይ ከሚሰሩ የዘርፉ አልሚዎች ጋር በትብብር ለመስራት ፍላጎት አላት። ማዕድን አልዎቹ የሚያነሷቸው ጉዳዮች ላይ በመምከር የሀገሪቱን ጥቅም ባስከበበረ መልኩ ወደተግባር እንዲገባ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው።

# የዞኑ አርሶ አደሮች በኩታ ገጠምና ጥምር ግብርና ዘርፍ ተጠቃሚ እየሆኑ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዶላ፡- በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን በኩታ ገጠም እርሻ እና ጥምር ግብርና ዘርፍ የተከናወኑ ሥራዎች አርሶ አደሩ ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረጋቸው ተጠቆመ።

የኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በጉጂ ዞን በአዶላ ሬዴ ወረዳ በምጪጫ ቀበሌ በመገኘት በኩታ ገጠም የተዘራ የበቆሎ ሰብል ላይ የመስክ ምልከታ አድርገዋል።

የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት ዋና አፈጉባዔ ወይዘሮ ሰዓዳ አብዱራሃማን እንደገለጹት፤ በዞኑ የኩታ ገጠምና የጥምር ግብርና እርሻ አርሶ አደሩን ይበልጥ ተጠቃሚ እያደረገው ነው። በዞኑ ያለው የግብርና ልማት እንቅስቃሴ በክልሉ የተያዘውን እቅድ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማሳያ ነው።

በተለይ በአዶላ ሬዴ ወረዳ በርብርብ ተሰርቶ የተገኘው ውጤት በሌሎች ቦታዎች እንዲደገም ለአርሶ አደሩ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ዋና አፈጉባኤዋ አክለውም፤ በዞኑ በኩታ ገጠም የተዘራው የበቆሎ ሰብል የሚያስፈልገው ግብዓት ተሟልቶለት በመዘራቱ ምርታማ መሆን እንደሚቻል የሚሳይ ነው ብለዋል።

ዞኑ በቅርብ ጊዜያት ከፍተኛ ድርቅ አጋጥሞት እንደነበር ያነሱት ወይዘሮ ሰዓዳ፤ በድርቅ ምክንያት ያጋጠመውን ችግር ለመቅረፍ አርሶ አደሩ እንዲበረታታ በክልሉ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ እንደነበር አብራርተዋል።

የጉጂ ዞን ዋና አስተዳደር አቶ ነጋሽ አላላ በበኩላቸው፤ ጥምር ግብርናውና አርሶ አደሩ በርብርብ እየሠራ ያለው ኩታ ገጠም እርሻ የሚጠበቀውን ውጤት እያስገኘ ነው ብለዋል።

አርሶ አደሩ የሚጠቀመውን የኩታ ገጠም እና ጥምር ግብርና ልምድ እያሳደገ ይገኛል ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ በኩታ ገጠም እርሻው እስከ 36 ኩንታል በቆሎ በሄክታር ለማግኘት እቅድ መያዙን ጠቁመዋል። ዞኑ በግብርናው ዘርፍ በዓመት ሦስት ጊዜ ምርት የመስጠት አቅም እንዳለውም ነው ያስረዱት።

እንደ አቶ ነጋሽ ገለጻ፤ በሰብል ዘር የተሸፈነው የበቆሎ ማሳ ተንከባክቦ ለምርት ከማድረስ የተለያዩ የሰብል በሽታዎች እንዳያጠቁት ትኩረት ተደርጓል። በተጨማሪም ብቃቱ ባላቸው ባለሙያዎች ለአርሶ አደሮች ስልጠና እንዲሰጡ እየተደረገ ይገኛል።

በዞኑ ከ72 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በክላስተር ተደራጅቶ በቆሎ፣ ስንዴ ቦሎቄ እየለማ ይገኛል ያሉት ደግሞ የጉጂ ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ታደሰ ብዙነህ ናቸው።

በተለይ በቆሎ እና ቦሎቄ አብሮ በመዘራት ጥምር ግብርናውን በማጎልበት ምርትና ምርታማነት ማሳደግና የአፈር ለምነት መጠበቅ መቻሉን ገልጸዋል።

## ዩኒቨርሲቲው ለአፍሪካ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተለያዩ ዘርፎች ብቁ የሰው ኃይልን በማፍራት ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካ ሀገራት አየር መንገዶች የሚመጥኑ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዚህም ዩኒቨርሲቲው ከኢትዮጵያ አልፎ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎችን በአቪዬሽን ዘርፍ እያሰለጠነ መሆኑን ገልጸው፤ ሥራ ከጀመረ አንስቶ ከተለያዩ የውጭ ሀገራት ከሁለት ሺህ በላይ ዜጎችን ማሰልጠኑን ተናግረዋል።

አየር መንገዱ ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች ተጠቅሞ የራሱን የሰው ኃይል በራሱ ማስተማርና ማብቃት የሚችል ትልቅ ድርጅት ነው ያሉት ስራ አስፈጻሚው፤ አየር መንገዱ ብቁ የሰው ኃይልን በማፍራት በአቪዬሽን ዘርፉ ራሷን የምትችል አፍሪካን እውን ማድረግን ግብ አድርጎ እየሠራ ነው ብለዋል።

እ.ኤ.አ በ2035 የአውሮፕላኖችን ቁጥር 270፣ መንገደኞችን 67 ሚሊዮን የበረራ መዳረሻዎችን ደግሞ 209 ለማድረስ የታቀደ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ ልክ የሆነ ብቁ የሰው ኃይልን ለማፍራት እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በቀጣይም ሀገሪቱ የውጭ ገቢ የምታገኝበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠርና የተለያዩ ግብዓቶችን ማምረት ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ያለው የግብዓት አቅርቦትና ብቁ ባለሙያዎች አለመኖር እየፈተነ ከመሆኑ የተነሳ፤ በዘርፉ የአውሮፕላን አብራሪዎችን ጨምሮ በርካታ ሙያተኞችን በማሰልጠን ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ችግሮችን ለመፍታት እየሠራ ነው።

የኢትዮጵያ አቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት አቶ ካሴ ይማም በበኩላቸው፤ ዩኒቨርሲቲው በአውሮፕላን አብራሪነት፣ በበረራ መስተንግዶ፣ በንግድና በአውሮፕላን ጥገና ዘርፍ ያሰለጠናቸውን 787 ተማሪዎች ማስመረቁን አስታውቀዋል።

ዩኒቨርሲቲው በዘርፉ ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ከኢትዮጵያ አልፎ ለሌሎች ሀገራትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ገልጸው፤ በልዩ ልዩ የአቪዬሽን ሙያዎች ያስመረቃቸው 878 ተማሪዎች ኢትዮጵያን ጨምሮ ከስምንት የአፍሪካ እና ከአንድ የእስያ ሀገር የተውጣጡ ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

በቀጣይም ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በልዩ ልዩ የአቪዬሽን ዘርፎች ብቁ የሰው ኃይል በማፍራት ለዘርፉ እድገት እንሠራለን ብለዋል።

## ስምንት ነጥብ ስድስት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ማንደፍሮ ንጉሤ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ኩታ ገጠም እርሻን ማስፋፋት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው።

በዚህም አርሶ አደሮች በ11 ሰብሎች በኩታ ገጠም እየሠሩ ነው ያሉት ዶክተር ማደፍሮ፤ ከነዚህ ውስጥ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ሰሊጥ፣ አኩሪ አተርና የቢራ ገብስ ተጠቃሽ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከፍራፍሬም አቮካዶ፣ ማንጎ እና ሙዝ እንዲሁም ከአትክልት ቲማቲም እና ሽንኩርት በኩታ ገጠም እየለሙ መሆኑን ተናግረዋል።

የኩታ ገጠም እርሻን የማልማት ሂደት አርሶ አደሮች በተመሳሳይ ጊዜ የማረስ፣ ዘር የመዘራት፣ የግብርና ምርትን የሚያሳድጉ ግብዓቶችን በጋራ የመጠቀም እድል የሚፈጥር ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የሳይንስ ምክረ ሃሳብ ይዘው የሚሠሩ በመሆኑ እንደ ሀገር ምርት እንዲጨምር ያደርጋል ብለዋል።

ኩታ ገጠም ላለፉት አምስት ዓመታት እንደተሠራበት ተናግረው፤ በኩታ ገጠም የሚለሙ ማሳዎች በግል ከሚለሙ ማሳዎች ጋር በንጽጽር ሲታዩ ትልቅ የምርት ልዩነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

በኩታ ገጠም የማምረት ሂደት ሜካናይዜሽን እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ኢንስቲትዩቱ የመካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላትን በ10 ቦታዎች ላይ ማቋቋሙን ተናግረዋል።

እንደ ማንደፍሮ (ዶ/ር) ገለጻ፤ የአገልግሎት ማዕከላቱ የጋራዥ አገልግሎት፣ ቴክኒሻኖችን የማሠልጠን፣ ማሽነሪዎችን የማከራየት እና በግላቸውም ይሁን በቡድን ጥራት ያላቸው የግብርና ማሽነሪ የመለዋወጫ እቃዎችን በማምጣት የሽያጭ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

ኢንስቲትዩቱ አርሶ አደሮች ምርታቸውን የሚሸጡበት የገበያ ማዕከላት እንደሚገነባ ተናግረው፤ በግብርና ግብዓት ዙሪያ 325 የአንድ መስኮት አገልግሎት ማዕከላት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን ተናግረዋል።

በመስኖ ልማት አንድ ጊዜ የሚመረተውን ምርት ወደ ሁለት ጊዜ ለማሳደግ እንዲቻል የከርሰ ምድር ውሃ ጥናት በ214 ወረዳዎች መጠናቀቁን አንስተው፤ ትግበራው በሙከራ ደረጃ መጀመሩንና በሂደት እየተስፋፋ እንደሚሄድ አስረድተዋል።

አርሶ አደሮች በአጠቃላይ ግብርናውን በተመለከተ ከግብዓት፣ ከማምረት እና ከግብይት ጋር ተያይዞ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ምክረሃሳብ በአካል እንዲሁም በዲጂታል መንገድ እንዲያገኙ እየተደረገ ነውም ብለዋል።

8028 ላይ በመደወል ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ እስከ ምርት መሰብሰብ ድረስ ያለውን ሂደት ማማከር እንደሚችሉ አመላክተው፤ 6077 ላይም በመደወል በየአካባቢው ያለውን የምርቶች አሁናዊ ዋጋ ማወቅ እንዲችሉ መደረጉን ጠቅሰዋል። ሰባት ሚሊዮን አርሶ አደሮች አገልግሎቱን እየተጠቀሙ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል።

## ኢድ አል አድሃ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ገልጸው፤ አቅሙ ያልፈቀደ በኢስላማዊ አስተምህሮው መሠረት በሶላትና በጸሎት በዓሉን እንደሚያከብር ተናግረዋል።

ምዕመኑ ከበዓሉ ሶላት መልስ አቅሙ በፈቀደው መጠን የእርድ ሥነ ሥርዓት እንደሚካሄድ ጠቅሰው፤ የእርዱን አንድ ሶስተኛ ለቤተሰቡ የቀረውን በአካባቢው ከሚገኙ ችግረኞችና ከጎረቤቶች ጋር በመቋደስ እንደሚከበር ገልጸዋል።

በዓሉን አቅም ያጠራቸውን ወገኖች በማሰብ ማክበር እንደሚገባ ገልጸው፤ እንደ ኢትዮጵያዊያን የመረዳዳት ባህልን የሚያጎለብት መሆኑን ጠቁመዋል።

እስልምና ጉርብትና መጠናከር እንዳለበት አጥብቆ ያዛል ያሉት ሀሰን አሊ፤ ኢትዮጵያዊ አብሮነታችንን ማጎልበት ትልቁ የእስልምና እሴት ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚና የሕግ ዘርፍ ተጠሪ ሳቢር ይርጉ በበኩላቸው፤ አረፋ ተካፍሎ በአብሮነት የሚበላበት የመተሳሰብና የትብብር በዓል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢድ አል አድሃ (አረፋ) የእርድ በዓል በመሆኑ የነቢይ ኢብራሂምና ኢስማኤል ታሪክ ያለበት ነው ያሉት ሳቢር ይርጉ፤ ኢስላማዊ አስተምህሮቱን ተከትሎ የእርድ ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል ብለዋል።

ለበዓሉ የታረደው ከብት ለሦስት ተከፍሎ ከፊሉን ቤተሰብ ጎረቤትና ሚስኪኖች እንደሚሰጥ ጠቅሰው፤ አረፋ ተካፍሎ በአብሮነት የሚበላበት የመተሳሰብና የትብብር በዓል መሆኑን ገልጸዋል።

ለኢትዮጵያውያን ተካፍሎ መብላት ባህል መሆኑን አንስተው፤ የአረፋ በዓል መተባበርና መደጋገፍን የሚያጎለብት እና የኢትዮጵያዊነት ማሳያ መሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

የአረፋ ሶላት እስኪሰገድ ድረስ ጾም መሆኑን ጠቅሰው፤ ከሶላት በኋላ ወደየቤቱ በመሄድ የእርድ ሥርዓት እንደሚፈጸምና ተካፍሎ የሚመገብ መሆኑን አስረድተዋል።

በአዲስ አበባ ስታዲየም በተከበረው በዓል ላይ የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን አማን ኤባን ጨምሮ ኡስታዞች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እና በርካታ የእምነቱ ተከታዮች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አስተማሪ መልዕክት!

ይቅርታ መጠየቅ ከሰብአዊ ማንነት የሚመነጭ የትህትና መገለጫ ነው። በተለይም ከፍ ባሉ ማኅበራዊ ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶች በተገነባ ማህበረሰብ ውስጥ በእለት ተእለት ህይወት ያለ ትልቅ ሰብአዊ እሴት ነው። እንደ ሰው ፍጹም አለመሆንን ፣ ከስህተት ለመማር ዝግጁ መሆኑንም ይገልጻል፡፡

የሰው ልጅ በፍጥረቱ ፍጹም ካለመሆኑ ጋር በተያያዘ የዕለት ተዕለት ሕይወቱ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በሚፈጠሩ ስህተቶች የተሞላ ነው። እነዚህ ስህተቶቹ በየትኛውም ሁኔታ ይፈጠሩ፣ የትኛውም አይነት ትርጓሜ እና ማብራሪያ ይሰጣቸው ተጨባጭ ከሆነ እውነታ ጋር የሚያስማማው ይቅርታ ነው።

ይህን ታሳቢ በማድረግም የይቅርታ ጉዳይ በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በግለሰቦችም፣ በቡድኖችም ሆነ በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ላለመግባባት ምክንያት የሚሆኑ ስህተቶች ወደ ኩርፊያና የግጭት ምዕራፍ እንዳይሻገሩ የጎላ ፋይዳም ይኖረዋል።

በተለይም በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውንም ሆነ ሊኖር የሚችለውን ሰላማዊ ግንኙነት አስጠብቆ በማስቀጠል፤ በሕዝብ ዘንድ የተሻለ ተቀባይነትን ለማግኘት በመንግሥት በኩል የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ ከፍያለ ስፍራ የሚሰጠው፤ ለሚመራው ሕዝብ ያለውን ከበሬታ የሚገልጽበትም አንዱ መንገድ ነው።

መንግሥት እንደ ተቋም የውሳኔ ሰጪ ግለሰቦች ስብስብ ነው፤ እነዚህ ግለሰቦች ሰው እንደመሆናቸው መጠን በግልም ይሁን በጋራ በሚደርሱባቸው ውሳኔዎች ስህተቶችን ሊሠሩ ይችላሉ። ብዙ ፍላጎቶች ባሉበት ማኅበረሰብ ውስጥ ደግሞ ይህ አይነቱ ሁኔታ የተለየ ገጽታ ሊሰጠው ይችላል፤ ለተለያዩ ትርጓሜዎችም ሊጋለጥ ይችላል።

በለውጥ ወቅት ከሚፈጠር ማኅበረሰባዊ /ሀገራዊ/ መሻት አንጻር በመንግሥት በኩል የሚቀርቡ ሕዝብን ይቅርታ የመጠየቅ መልካም አካሄዶች፤ በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለው የሕግ እና የሞራል መስተጋብር ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥል ከማስቻል ባለፈ በለውጡ ተስፈኛ የሆነው ሕዝብ በመንግሥት ላይ ያለውን አመኔታ ጠብቆ ማስቀጠል እንዲቻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ሕዝቡ የለውጡ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን መንግሥት ለውጡን በተሻለ የባለቤትነት መንፈስ ማስቀጠል የሚያስችለውን አመኔታ ይፈጥርለታል፤ ካልተገባ ኩርፊያ እና ከለውጥ የመነቃቃት መንፈሱ እንዳይቀዛቀዝ ትልቅ ጉልበት ሊፈጥርለትም ይችላል፤ ከሁሉም በላይ የመንግሥት ሹመኞች ሊሳሳቱ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለና ለዚህ ስህተታቸውም ይቅርታ መጠየቅ የሚችል ሰብአዊ ማንነት እንዳላቸው ያመላክታል።

በርግጥ እኛ ኢትዮጵውያውያን በዘመናት በትውልዶች መካከል የተፈተነ እና እንደ ሕዝብ በመላው ዓለም እወቅና ያስገኙልን የብዙ ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ባለቤቶች ነን። ከይቅርታ ጋር የተያያዘው ማህበረሰባዊ ማንነታችንም ቢሆን የዚህ እውነት አንድ አካል ተደርጎ ይወሰዳል።

የግለሰባዊ ፣ ቡድናዊም ሆነ ማህበራዊ አለመግባባቶች ምንጭ የሆኑ ስህተቶችን በይቅርታ ማለፍ በዘመናት ውስጥ የዳበረው የእርቅ ባህላችን ዋንኛ መገለጫም ነው። የሀገሪቱ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ይቅርታ ለመጠየቅም ሆነ ለመቀበል ሰፊ ልብ ያላቸው ናቸው ። ይህም በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ተደጋግሞ የሚስተዋል እና የሚበረታታ ማህበራዊ እሴት ነው።

ይህም ሆኖ ግን ከዚሁ ማህበረሰብ እሴት ውስጥ የሚገነባው የሀገሪቱ ፖለቲካ ሥርዓትም ሆነ ሥርዓቱን የሚፈጥረው የፖለቲካ ስብእና ይቅርታ ለመጠየቅም ሆነ ለመቀበል የተከፈተ ልብ የሌለው ሆኖ ቆይቷል። ከዚህ ይልቅ ይቅርታ መጠየቅን እንደ ትልቅ ውርደት እና ሽንፈት አድርጎ ሲወስድ ኖሯል።

ከዚህ የተነሳም በሀገሪቱ የፖለቲካ ባህል ውስጥ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ ያልተለመደ ፣ በሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የማይታሰብ ሆኖ ዘመናት ተቆጥረዋል። በዚህም በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት ከኃይል ባለፈ ይቅርታ በሚወልደው ትህትና የመቃኘት እድል ሳያጋጥመው ዘመናትን ተሻግሯል።

ይህም ሕዝቡ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ውሳኔ ሰጪ ግለሰቦችን /ሹማምንቶችን/ ለሁሉም ነገር አልፋና ኦሜጋ አድርጎ የማየት የተሳሳተ ማህበራዊ ቅኝት እንዲኖረው አድርጓል፤ እነዚህ ውሳኔ ሰጪ ግለሰቦች /ሹማምንቶች/ ከሕዝቡ የሚጋሩትን ትልቁን ማህበራዊ እሴት እንዲያጡም አድርጓቸዋል። ይህ የተዛባ ማህበረሰባዊ እሳቤ በመንግሥት እና በሕዝቡ መካከል ያለውን የሕግ እና የሞራል መስተጋብርም ጤናማ እንዳይሆን አድርጎታል።

ይህን እንደ ጥላ ሲከተለን ዘመናት ያስቆጠረ ሀገራዊ /ማህበረሰባዊ/ ችግር ለመሻገር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከኮሪደር ልማቱ ጋር በተያያዘም ሆነ በሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች በየትኛውም ምክንያት ሊፈጠሩ ለሚችሉም ሆነ ለተፈጠሩ ስህተቶች ሕዝብን በአደባባይ ይቅርታ መጠየቃቸው ትልቅ ጅማሬ፤ ከፍያለ እውቅና ሊሰጠው እና ሊበረታታ የሚገባ ተግባር ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢድ አል አድሃ በዓልና ኢትዮጵያዊ እሴቶች

እስማኤል አረቦ

የአረፋ በዓል ታላቅ በዓል ነው። የእስልምና እምነት እንደሚያስተምረው አረፋ የሚለው ቃል በአረብኛ "አወቀ" እንደማለት ነው። ይህም ታሪክ አለው። አዳምና ሔዋን ወይንም አደምና ሃዋ ከጀንነት ወደ ምድር ከወረዱ በኋላ ለብዙ ዘመናት ተጠፋፍተው ነበር። ለረጅም ጊዜ ሲፈላለጉ ከቆዩ በኋላ በዚህ ዕለት በሳዑዲ አረቢያ ባለው የአረፋ ተራራ ላይ ተገናኙ። እዚያም "ዐረፍቱከ… ዐረፍቱኪ" ተባባሉ። "አወቅኩህ! አወቅኩሽ" ማለታቸው ነው። ይህንን ታሪክ ለመዘከር ሲባል ነው የአረፋን በዓል ማክበር የተጀመረው፤ ይህ በዙልሂጃ ዘጠነኛው ቀን የሚከበር በዓል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢድ አል አድሃ ወይም አረፋ ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸው እስማኤልን በአላህ ትእዛዝ ለመስዋዕት ሲያዘጋጁ በምትኩ ሙክት በግ መቅረቡን የሚያስታውስ በመሆኑ የመስዋዕት በዓል ተብሎም ይከበራል።

ኢድ አል አድሃ የመተሳሰብና የመረዳዳት በዓል ከመሆኑም ባሻገር ሙስሊሞች የመስዋዕትነት በዓሉን እርድ በመፈጸም፣ በጋራ በመጸለይ እና ከፈጣሪ ምህረትን የሚያስገኙ በጎ ተግባራትን በማከናወን ያሳልፉታል።ይህም ያጡ ወገኖች የሚደገፉበትና መረዳዳትና መደጋገፍ የሚታይበት በመሆኑ በዓሉ የተለየ ገጽታ ይዞ ይከበራል።

ኢድ አል አድሃ የነብዩ ኢብራሂምና ልጃቸውን የእስማኤልን ታሪክ መነሻ በማድረግ ኢድ ይከበራል። በዓሉ የመስዋዕት፣ የእርድ በዓል ነው። በተለይም የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ቀን ከብት የማረድ ግዴታ አለበት። የተቀረውም ሙስሊም ዕለቱን አቅሙ በፈቀደ ከብት በማረድ ከቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ጋር ያሳልፈዋል። ለኢድ አልአድሃ አንድ ሰው ከሚያርደው ከብት ሲሶውን ብቻ ለራሱ እንዲወስድ ነው ደንቡ። የተቀረው ሲሶው ለዘመድ አዝማድ፣ ሲሶው ደግሞ አቅም ለሌለው ድሃ እንዲከፋፈል እስልምና ያዛል።

ይህንንም መሠረት በማድረግ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባም ሆነ በተለያዩ አካባቢዎች በበዓሉ ዕለት ሰዎች ድሃ ጎረቤቶቻቸውን ይዘይራሉ፤ ያላቸውን ያቋድሳሉ፤ የታረዙትን ያለብሳሉ፤የተጠሙትን ያጠጣሉ።በተለይም ወላጅ አልባ ሕፃናት ከፍተኛ ትኩረትና እንክብካቤ ያገኛሉ። ስለዚህም በዓሉን ተደስተው ያሳልፋሉ።

ከዚሁ ጎን ለጎንም በበዓሉ ዕለት ሙስሊሞች ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸውን በመጥራት እና ማዕድ በመቋረስ በዓሉን በድምቀት ያሳልፋሉ።ስለሀገራቸው ሰላምና አንድነት ይጸልያሉ፤ አብሮነታቸውንም ያጠናክራሉ።

አረፋ የአብሮነት በዓል ነው። በአረፋ በዓል ወዳጅ ዘመድ ተሰባስቦ በዓሉን በጋራ ያሳልፋል፤ አብሮነት ይደምቃል። ከዚህ ባሻገር ግን ከጥንት በኢትዮጵያ ያለው የአረፋ በዓል አከባበር ለየት የሚልባቸው እሴቶች አሉት።ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ እምነቶችን በፀጋ የተቀበለችና የተለያዩ እምነት ተከታዮችም ተከባብረው የሚኖሩባት የተለየች ሀገር ነች። አረፋን በመሳሰሉ የበዓል ወቅት ደግሞ በክርስትና በዓላት እንደሚደረገው ሁሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ጎረቤቶችን በመጥራት በዓሉን በጋራ ማሳለፍ የተለመደ ነው። ይህ አንዱ ኢትዮጵያዊ ዕሴት ሲሆን፤ ለዘመናትም ሲወርድ ሲዋረድ ዛሬ ላይ የደረሰ ድንቅ መገለጫችን ነው።

ነብዩ ኢብራሂም በእስልምና ሃይማኖት በነበራቸው አስተምህሮት የሰው ልጆች ያለ ዘርና ሃይማኖት ልዩነት የምድር ፍጡራን ሁሉ እኩል መሆናቸውን ሲያስተምሩ የቆዩ በመሆኑ ዛሬ በዘር፣ በጎሳና በሃይማኖት ልዩነት እየተናጠች ለምትገኘው ሀገራችን አስተምህሮቱ ከፍተኛ ትምህርት ይሰጣል። ሕዝበ ሙስሊሙም ልዩነትን፣ መገፋፋትና መወቃቀስን በማስወገድ ለሀገሩ አንድነትና ሰላም የሚሰራበት ወሳኝ ወቅት ላይ እንደሚገኝ መረዳት አለበት።

በተለይም ነብዩ ኢብራሂምና ልጃቸው እስማኤል ያሳዩት ታዛዥነት ለዛሬው ትውልድ ከፍተኛ ትምህርት ይሰጣል።ታናሽ ለታላቁ ታዛዥ መሆን አለበት፤ ሕዝብ ለመሪዎች ታዛዥ መሆን አለበት፤ ምዕምናን ለሃይማኖት አባቶች ታዛዥ መሆን አለባቸው።ይህ ሲሆን ፉክክር ይጠፋል፤ በምትኩም መተዛዘንና መረዳዳት ይነግሳል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት አንዱ የበዓሉ ዕሴት ነው። የእስልምና እምነት ድሆችን ማብላትና ማጠጣት እንዲሁም በዓላትን እኩል በደስታ እንዲያሳልፉ በአማኞች ላይ ግዴታ ጥሎባቸዋል።ከእነዚህ ትዕዛዞች አንዱ ያጡና የተቸገሩ ወገኖች መርዳትና መደገፍ አንዱና ዋነኛው ነው።

የእምነቱ ተከታዮች በዓላትን እራሳቸው ብቻ ተደስተው እንዲያሳልፉ አይፈቀድላቸውም።ይልቁንም በዓላት ድምቀት የሚኖራቸውና በፈጣሪም ዘንድ ተቀባይነትን የሚያጎናጽፉት ከተቸገሩ ወገኖች ጋር አብሮ ማሳለፍ ሲቻል ነው።ስለዚህም ሙስሊሞች የመውሊድ በዓልን ሲያከብሩ ለተቸገሩ ወገኖች ማዕድ ከማጋራት ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ሊሆን ይገባል።

በአጠቃላይ መውሊድ የመረዳዳት በዓል በመሆኑ ከዚህ በሻገር እንደሀገር ትልቅ ፋይዳ ያለው በዓል ነው።በተለይም በአሁኑ ወቅት በጸጥታ ችግር ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና የተሰደዱ በርካታ ወገኖች አሉ። ከዚሁ ባሻገር በድርቅ የተጎዱና በተለይ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ጦርነት ካሳደረባቸው ጠባሳ ያላገገሙ ወገኖች በችግር ውስጥ ስለሚገኙ እነዚህን ወገኖች መደገፍና ተባብሮ ወደ ቀድሞ ህይወታቸው መመለስ አንዱ በመውሊድ ወቅት የሚከወን ተግባር ሊሆን ይገባል።

በአረፋ መረዳዳትና መደጋገፍ ቢስተዋልም በዚህ ወቅት የሚስተዋለው መደጋገፍ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የሚከናወን ተግባር ሊሆን ይገባል። የደካሞችን ቤት በማደስ፣ ለጦም አዳሪዎች የዕለት ጉርሳቸውን ማቅረብ ፣ የታረዙትን ማልበስና ወላጅ አልባዎችን መጎብኘት በኢድ አልአድሃ የሚወደድ ተግባር ቢሆንም በሌሎችም ቀናት እነዚህ በጎ ተግባራት ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው ናቸው።

ማኅበረሰቡ በበዓል ወቅት ከመረዳዳት ባሻገር ሀገራዊ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በጋራ መቆምም ይጠበቅበታል።ሰዎች በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ጉዳት ሲደርስባቸው፣ ከአካባቢያቸው ሲፈናቀሉ፣ ሲራቡና ሲጠሙ ዝም ብሎ መመልከት ከእስልምና አስተምሮ አንጻር የሚያስጠይቅ ነው። በተለይም ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ስንመለከት በርካቶች ቤት ንብረታቸውን ጥለው የተሰደዱበትና የተፈናቀሉበት ሁኔታ ነው ያለው። ስለዚህም የኢድ አልአድሃ በዓልን ስናከብር እነዚህን ወገኖች በመጎብኘትና ወገናዊ ፍቅር በመስጠት ሊሆን ይገባል።

አሁን አሁን የድሆችን ቤት በማደስ፣ማዕድ በማጋራትና የተጀመሩ ሥራዎች የሚያስደስቱ ናቸው።እስልምና በጣም የሚደግፋቸውና አብዝቶም የሚሠራባቸው ናቸው። ወቅቱ ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ መረዳዳት የሚያስፈልግበት በመሆኑ የተለያዩ ድጋፎች ለተፈናቃዮችና ችግር ለደረሰባቸው ሰዎች ማድረስ የግድ ይላል።

በእርግጥ በአሁኑ የመተሳሰብ ፣የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጠናክሮ ቀጥሏል።በተለይም አቅመ ደካማ ለሆኑ ዜጎች ማዕድ ማጋራትና ድሃ ድሃ ቤት እድሳት በዚህ ረገድ ተጠቃሾች ናቸው።ይህ አኩሪ በዓልም በኢድ አልአድሃ አረፋ በዓል!

የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።መጪው ጊዜም የክረምት ወቅት እንደመሆኑ መጠን የበጎ ፈቃድ ሥራዎች የሚበራከቱበት ነውና አኩሪ የሆኑ እሴቶቻችን ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

**መልካም የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል!**

## ነፃ ሃሳብ

# ለኮሚሽኑ ዓላማ ስኬታማነት ...

ሰው መሆን

ኢትዮጵያ ሺህ ዓመታትን የተሻገረ ሀገረ መንግሥት የገነባች ሀገር ነች። ይሁን እንጂ የሀገረ መንግሥት ግንባታው የተጠናቀቀና ምሉእ አይደለም። በየዘመናቱ በትውልድ አለመግባባት፣ በተሳሳተ ትርክትና በመሳሰሉት እንቅፋቶች ጠንካራ መሠረት የመጣል ሂደቱን የሚያስተጓጉሉ ችግሮችንም እየተጋፈጠች እና መፍትሄዎችን እያስቀመጠች ነው ሉዓላዊት ሀገርነቷን አስጠብቃ እዚህ መድረስ የቻለችው። ዛሬስ?

ዛሬም የኢትዮጵያውያንን አንድነት የሚፈታተኑ፣ የሀገረ መንግሥቱን ጥንካሬ ለመናድ የሚግደረደሩ፣ የማህበረሰቡን አብሮ የመኖር እሴት የሚያዳክሙ አያሌ የውስጥና የውጭ ፈተናዎችን እየተጋፈጠች ትገኛለች። እነዚህ ችግሮች ባለፉት ዓመታት የሀገሪቱን ህልውና የተፈታተኑ ፣ የሕዝቦችን እምነት የሸረሸሩ፣ ጥርጣሬና አለመግባባት ያነገሡ ነበሩ። ችግሮቹ ግን ከኢትዮጵያውያን አንድነት፣ መተባበር፣ ጥንካሬና ፈተናዎችን በብልህነትና በጥበብ በጋራ ከማለፍ ባህል በላይ አይደሉም።

ለዚህ ነው ባለፉት 6 እና ከዚያ በላይ በነበሩ ዓመታት ኢትዮጵያውያን ባጋጠማቸው የውስጥ ችግርና ፈተና ሳይሰበሩ በሁለት እግራቸው መቆም የቻሉት። ከዚያም በላይ ለዘመናት የቆዩ የተዛቡ ትርክቶችን፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈጠሩ ግጭቶችን እና ሌሎች የፍትሃዊነት እና በእኩልነት በጋራ የመኖር ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ የማያዳግም መፍትሄ ለመስጠት በጋራ ለመምከር የወሰኑት።

ኢትዮጵያውያን ጎራ ለይተው ከሶስትና አራት ዓመታት በፊት ገብተውበት በነበረው የለየለት ግጭትና ቀውስ ያተረፉት፤ ውዱን የሰው ልጅ ሕይወት ማጣት፣ የንብረት ውድመትና የተዳከመ ኢኮኖሚ ውስጥ መዘፈቅ ነው። ለዚያም ነው ሰከን ወዳለው፣ በውይይትና በምክክር መፍትሄን ማምጣት ወደሚቻልበት የጠረጴዛ ዙሪያ ለመምጣት መንገዱን የጀመሩት። ለዚያም ነው በግጭትና ጦርነት ሳይሆን በምክክርና በውይይት የሚገነባ ጠንካራ ሀገረ መንግሥት እንደሚያስፈልግ አምነው የሃሳብ ልዩነቶቻቸውን ለማስታረቅ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ያቋቋሙት።

ዛሬም ሁሉም ኢትዮጵያውያን (የፖለቲካ ሃይሉ፣ ባለሀብቱ፣ የግልና የመንግሥት ተቋማት፣ ግለሰብ ተፅእኖ ፈጣሪዎች፣ ወጣቶች ሴቶችና ወዘተ) በግጭት፣ በጉልበት አሊያም በውጭ ጣልቃ ገብነት የሚያገኙት ዘላቂ መፍትሄ እንደሌለ ሊገነዘቡ ይገባል። ይህንን እውነታ የተረዱ ብዙሃን ቢኖሩም ጥቂት የማይባሉ ሃይሎች ግን አሁንም ድረስ ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ ለሚደረገው ውይይት ዝግጁ አይመስሉም። ይህንን ችግር መፍታት እና ተከታታይ ውይይቶችን በማድረግ ወደ ምክክሩ የሚካተቱበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል።

በተለይ እነዚህ ሃይሎች የሚያነሷቸውን ቅስመ ሁኔታዎች በማጤን፣ ፍላጎቶቻቸውንና ጥያቄዎቻቸውን ቀረብ ብሎ ለመገንዘብ በመሞከር ሁሉንም ሃይል የሚያካትት ምክክር ለማድረግ ወደ መፍትሄው መቅረብ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ሆደ ሰፊነትና ታጋሽነት መርህ ሊሆን ይገባል።

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑን የሚመሩት አካላት ላለፉት ዓመታት ተከታታይ ሥራዎችን ሲያከናውኑ እንደነበር ተመልክተናል። ተሳታፊ ሃይሎችን በመለየት፣ አጀንዳዎችን በማሰባሰብ፣ ምክክር የሚመራበትን ሕግ፣ ፖሊሲ ከሚያወጡ አካላት ጋር በጋራ በመሥራት ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን በተከታታይ በሚወጡ የመገናኛ ብዙሃን መረጃዎች ላይ መረዳት ችለናል።

በተቃራኒው ደግሞ የምክክር ኮሚሽኑ የሚሠራቸውን ሥራዎች፣ ተግባርና ሃላፊነት በቅጡ ያልተረዱ (አሊያም ከግንዛቤ እጥረት ብዥታ ውስጥ የገቡ) አካላት ሂደቱን ሲተቹ፣ አንዳንዴም እንቅፋት ሲሆኑ ይስተዋላል። ይህንን ድርጊት በተመሳሳይ ብብልሃት እንዲሁም በሆደ ሰፊነት መመልከትና ዓላማውን ለሕዝብ በግልፅ በተከታታይ ማስገንዘብ ይገባል።

> **ኢትዮጵያውያን መክረው አንድ ጠንካራና ሉዓላዊ የሆነች ኢትዮጵያን መገንባት እንዲችሉ ለትውልድ እንዲያስተላልፉ እርስ በእርስ መተማመንና ጥርጣሬን ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል**

ኢትዮጵያውያን በጋራ ችግሮቻቸውን መፍታት እንዲችሉ፣ ዘላቂ የሆነች ሉዓላዊት ኢትዮጵያን (ሀገረ መንግሥት) እንዲገነቡ በራሳቸው እሴቶች፣ የመከባበርና የመደማማጥ ባህል እንዲሁም በውስጥ አቅም መወያየትና መፍትሄዎችን ማስቀመጥ እንደሚኖርባቸው ኮሚሽኑ የማሳመን ሥራዎችን ሊሠራ ይገባል። ከዚያም ባለፈ ሁሉም አካላት የሚሳተፉበት እንደሆነ በግልፅ የሚያሳዩ አደረጃጀቶች መፈጠራቸውን ማሳየት ያስፈልጋል።

ባለፉት ዓመታት ኮሚሽኑ መቋቋሙንና ወደ ሥራ መግባቱን ተከትሎ ብዥታን የሚፈጥሩ የተለያዩ መረጃዎች ሲወጡ ተመልክተናል። ለውጤታማነቱ እንቅፋት የሚሆኑ እነዚህን ጉዳዮች ሁሉም ተሳታፊ አካላትና ኮሚሽኑ ያለመታከት ማጥራትና ግንዛቤ መፍጠር ይኖርባቸዋል።

በምክክሩ ላይ ጥርጣሬን የሚያጭር መረጃዎች ከሚወጡባቸው ጉዳዮች መካከል ሁለት ጉዳዮች ዋና ዋና መሆናቸውን የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ያምናል። የመጀመሪያው አካታችነት (all inclusive) የሚለው ጉዳይ ሲሆን በዚህ ረገድ ኮሚሽኑ በምክክር ላይ የሚሳተፉ ሕዝባዊ መሠረት ያላቸው ማናቸውም ተቋማት፣ ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ የፖለቲካ አደረጃጀቶች፣ ምሁራን እና የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። መፍትሄ ይሻሉ ብለው የሚያነሷቸው አጀንዳዎች፣ የማህበረሰቡ ጥያቄዎችም መካተታቸው ማረጋገጥ እንዲሁ ተገቢ ነው።

ከሰሞኑ ከሰማናቸው ጉዳዮች መካከል ጠንካራ ሕዝባዊ መሠረት እያላቸው፤ ለሀገረ መንግሥት ግንባታና ለኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ ሌሎች እሴቶች ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ሃቅ ሆኖ ሳለ በዚህ ሀገራዊ ምክክር ላይ ተሳታፊ ለመሆን ጥሪ እንዳልተደረገላቸው በይፋ ግልፅ ቅሬታ እንደፈጠረባቸው የገለፁ አካላት እንዳሉ ነው። ለዚህ ምክንያታዊ ለሆነ ጥያቄ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ፈጣን ምላሽ እንደሚኖረው ቢታመንም ቅሬታው ሳይፈጠር በፊት መፍታት አለመቻሉ የፈጠረ ብዥታ ያደረሰውን ጉዳት አለመቀነስ መቻሉ እንደ ክፍተት ሆኖ ሊወሰድ ይገባል።

ምክንያቱም እራሱ ኮሚሽኑ እንደነገረን «አካታችነት እና ወካይነት» መሠረታዊው መርሁ ነው። ኮሚሽኑ በጀመረው የምክክር ምዕራፍ በበርካታ ቡድኖች፣ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ተቋማት እና ግለሰቦች የሚቀነቀኑ የተለያዩ ሃሳቦችን በተገቢው መንገድ በማካተት ለሂደቱ ስኬት እየሠራ እንደሚገኝም ገልፆልናል፡፡ በሂደቱ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በአግባቡ ወኪሎቻቸውን በመላክ በሀገራዊ ምክክር ጉባዔው ላይ እንዲንፀባረቅላቸው የሚፈልጓቸውን ሃሳቦች የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑ በተደጋጋሚ ቃል በቃል ሲገልፅ ሰምተናል።

በመሆኑም የኮሚሽኑ መርህ ይህ ሆኖ ሳለ ለምን ከላይ በስም ያልጠቀስናቸው አካላት እንዳልተካተቱ አሊያም በሂደቱ ላይ ቅሬታ እንዴት ሊፈጠርባቸው እንደቻለ አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ ያስፈልጋል። ከዚያ ባሻገር እነዚህን ብዥታዎች በተገቢው መንገድ በማጥራት ይገባል።

ሌላውና ሁለተኛው ጉዳይ በምክክሩ ላይ የሚሳተፉ የተለያየ የሃይል ሚዛን ያላቸው አካላት በሂደቱ ላይ የሚፈጠርባቸው የእምነት ማጣትና የጥርጣሬ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው በዚህ ምክክር ላይ የማይሳተፉ ጠብ መንጃን እንደ አማራጭ የቆጠሩ ሃይሎች አሉ። ከዚህ ባሻገር በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚገኙ በተመሳሳይ በዚህ መድረክ ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኝነት የጎደላቸው አይጠፉም። እነዚህ አካላት በምክክሩ ላይ ለመሳተፍ የማይፈልጉበትን ምክንያት ሲጠቅሱ ከሚያነሷቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መንግሥት በቁርጠኝነትና በፍፁም ቅንነት ምክክር ለማድረግ አይፈልግም የሚል ነው። በምክክሩ ላይ ተሳታፊ ለመሆን ወደፊት ቀርበውም ይህንን መሰል ጥያቄ የሚያነሱ አሊያም እምነት ማጣትና ጥርጣሬ የፈተናቸው ባለድርሻዎች በርካቶች ናቸው።

ኢትዮጵያውያን መክረው አንድ ጠንካራና ሉዓላዊ የሆነች ኢትዮጵያን መገንባት እንዲችሉ ለትውልድ እንዲያስተላልፉ እርስ በእርስ መተማመንና ጥርጣሬን ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በገለልተኛ ምሁራን እና ባለድርሻ አካላት የተቋቋመው ምክክር ኮሚሽን ሃላፊነት ሊወስድ ይገባል። ምንም እንኳን እየሠራ ያለው ሥራ ከእንከን የፀዳ ነው የሚል ግብታዊ ድምዳሜ ሁሉም ሊደርስ ባይችልም ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ግለሰብ ተፅእኖ ፈጣሪዎች እና ሌሎችን በተቋሙ ላይ የጋራ እምነት እንዲኖራቸው ተከታታይነት ያለው ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል።

ኮሚሽኑ ይህንን መሰል ጥርጣሬዎችን ለመቅረፍ ከዋና ዋና መርሆቹ መካከል «የባለድርሻ አካላትን ሃይል ማመጣጠን» አንዱና ዋነኛ ግቡ እንደሆነ ደጋግሞ ነግሮናል። በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የተለያየ የሃይል ሚዛን ያላቸውን ባለድርሻ አካላት እያሳተፈ እንደሚገኝ ግልፆ፤ ይህንኑ መነሻ በማድረግ የተለያየ የሃይል ሚዛን ያላቸውን አካላት በእኩልነት እንደ ባለድርሻ አካል በመቁጠር ሂደቱን እየመራና እያስተባበረ እንደሚገኝ በመገናኛ ብዙሃን አድምጠናል። ይህንን ርምጃውን ለተሳታፊ አካላት በተደጋጋሚ ማስረዳት ሥራዎችንም በግልፅነት ማከናወን ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ ሲቻል ከላይ እንደተቀመጠው ጥርጣሬንና እምነት ማጣትን የሚፈጥሩ ድርጊቶችን ቦታ እንዳይኖራቸው በተለያዩ አውታሮች የምንሰማቸው አሉባልታዎችም እንዲከስሙ ይሆናል።

ከላይ በዝርዝር ለማንሳት እንደሞከርነው ኢትዮጵያውያን ካለፉት ዘመናት ታሪኮቻቸው መረዳት እንደሚችሉት ተቀራርቦ በመነጋገር እንጂ በግጭት ሀገር ማፍረስ እንጂ መገንባት እንደማይቻል ነው። በቅን ልቦና ምክክር ለማድረግ፣ ልዩነት የፈጠሩ ትርክቶችን ለማረቅ እና ያዘነበለውን ለማቃናት መመካከር ምርጫ የሌለው መፍትሄ ነው። ለዚህ ነው እዚህም እዚያም የሚገኙ ፅንፎች በመካከላቸው የሚገኘውን ሰፊ ክፍተት ለማጥበብ ወደ ጠረጴዛው ዙሪያ መምጣት የሚጠበቅባቸው። ለዚህ ዓላማ ስኬት ደግሞ ስክነት እና ሆደ ሰፊነት መርሆች ናቸው። ኮሚሽኑ እየተገበራቸው የሚገኙ ሥራዎች ዳር የሚደርሱትም፣ እስካሁን የመጣንበት ውጥንቅጥም መቋጫና መቋጠሪያ የሚያገኘው በዚህ አግባብ ነው።

ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ከመንግሥት ጀምሮ ሁሉም የድርሻውን ጥረት ማድረግ ይገባዋል። ከሁሉ በላይ ግን ዛሬም ድረስ በዚህ አካሄድ እምነት ያጡና ሌሎች ዓሉታዊ አማራጮችን የተከተሉ ሃይሎች መንገዳቸውን ማጤን ይኖርባቸዋል። እነርሱ እንወክለዋለን የሚሉት የማህበረብ ክፍል፣ እንሰዋለታለን ያሉለት ዓላማ በጠብ መንጃ አፈሙዝ የሚሳካ ሳይሆን በቅንነት፣ በፍፁም ግልፅነት እና በጋራ ሆኖ መፍትሄ በመፈለግ መፍትሄ የሚያገኝ መሆኑን ማመን አለባቸው። የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ፣ መንግሥትና ሌሎች የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚያደርጉትን የምክክር ጥሪ መቀበል ይኖርባቸዋል። ይህ ሲሆን የሚጠፋ የሰው ሕይወት ሳይኖር፤ ሀብትና ንብረት ሳይወድም ጠንካራ ሀገረ መንግሥት መገንባት ይቻላል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ለዘላቂ የሌማት ቱሩፋት ምርታማነት- አስተማማኝ የገበያ አቅርቦት

ማህሌት አብዱል

ኢትዮጵያ የግብርና ዘርፉን ምርትና ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ፣ በተለይ ደግሞ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል ያለችውን የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር በመተግበሯ በዘላቂነት ሊለውጡ የሚችሉ ውጤቶችን ማስመዝገብ ጀምራለች። መርሃ ግብሩ በሀገር ደረጃ ማዕዶችን በብዛትና በዓይነት ሙሉ ከማድረግ ባሻገር ለሌሎች መትረፍን ያለመ ሲሆን፣ ለዚህም እምቅ ሀብቶችን የማልማትና የመጠቀም አቅጣጫን ተከትሏል። በዋናነትም የምግብ ዋስትና ችግርን ለመፍታት እና የሥነ ምግብ ሚዛን መዛባትን ለማስተካከል ፍቱን መፍትሔ እየሆነ መምጣቱንም የዘርፉ ተዋናዮች ይናገራሉ።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ የሌማት ትሩፋትን ባስጀመሩበት በወቅት፣ «ሌማት አርሶአደሩን አርብቶ አደሩንና ሸማቹን የሚያገናኝ ድልድይ ነው። በቂ እና አመርቂ ምግብ ማግኘትን ያለመ ነው። በቂ የመጠን፣ አመርቂ የይዘት ጉዳይ ነው፤ በምግብ ራስን መቻል ከሀገር ሉዓላዊነት ክብር ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው» ሲሉ ስለመርሀ ግብሩ ፋይዳ መናገራቸውም ይታወቃል።

በመርሀ ግብሩ ገና ከአሁኑ ለውጦች እየተመዘገቡ ስለመሆናቸው ከየክልሉ የወጡ መረጃዎችን ዋቢ ያደረጉ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች ያመለክታሉ። የመንግሥት ሃላፊዎችም፣ የግብርና ባለሙያዎች ይህንኑ እያረጋገጡ ይገኛሉ።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የግብርና እና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና ግብርና ቢሮ ሃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር እንዳሉትም፤ የሌማት ቱሩፋት በክልል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሀገር ደረጃ ተጨባጭ ውጤቶችን እያመጣ ነው። መርሃ ግብሩ እንደሀገር ከፍተኛ እጥረት የነበረባቸው የወተት ፣ ስጋ፣ እንቁላል፣ ማር፣ ዓሳ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ መሠረታዊ የሚባል ውጤት እያስገኘ ነው።

እንደሀገር በመርሀ ግብሩ የአርሶአደሩ የማምረት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን ይጠቅሳሉ። የአርሶ አደሩን ያመራረት ባህል ከመቀየር አኳያም ወሳኝ ሚና ተጫውቷል ሲሉ ይገልጻሉ፤ «በልማት ውስጥ የሚገቡ ሰዎች ቁጥር መጨመሩን፣ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ባለሀብቶችና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ሳይቀሩ መነቃቃት ተፈጥሮባቸው ልማቱን መቀላቀላቸውንም አመልክተዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያን ክልል ተሞክሮ ጠቅሰውም ሲያብራሩ፤ «አርሶአደሩ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ የክልሉ ነዋሪ በጓሮው አትክልትና ፍራፍሬ በማልማት፣ ዶሮና የተሻሻለ ዝርያ ባላቸው የወተት ላሞች በወተት ልማት እንዲሁም በንብ ማነብና በዓሳ እርባታ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል፤ ይህም የቤተሰቡን የተመጣጠነ ምግብ ፍላጎት ከማሻሻሉም ባሻገር በእነዚህ ምርቶች ላይ የነበረውን የዋጋ ንረት ከማርገብ አኳያ የላቀ ሚና እየተጫወተ ነው፤ ሌማታችን በዓይነትም በብዛትም እየተትረፈረፈ ነው ያለው፤ በዚህ መነሻ ተርቦ የነበረው ገበያ በአጭር ጊዜ ውስጥ በምርት ተጥለቅልቋል» ሱሉም ይጠቅሳሉ።

ከወራት በፊት ከ180 ብር በላይ የነበረው የቀይ ሽንኩት ዋጋ አሁን ላይ ወደ 40 ብር፣ ቲማቲም ከ100 ብር ወደ 20 ብር ወርደዋል። በሌሎችም የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የዶሮና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶች ላይ የዋጋም የመጠንም መሻሻል ታይቷሉ ሲሉ ጠቅሰው፣ የዚህ ሁሉ ስኬት መርሃ ግብሩ መሆኑን ገልጸዋል። ይህም የአርሶአደሩ የአመራረት ባህሉ መቀየሩን እንደሚያሳይ ተናግረዋል፤ «አትክልት በማይመረትባቸው አካባቢዎች ልማቱ መጀመሩ ሥነ-ምህዳሩ ሳይቀር እንዲቀየር ምክንያት ሆኗል። የሌማት ቱሩፋት እንደአጠቃላይ ተስፋም እድልም ይዞ መጥቷል» ሲሉ ይገልፃሉ።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ዳይሬክተር ዶክተር ታደለ ማሞ እንደሚሉት፤ የሌማት ቱሩፋት መሠረታዊ የሚባሉ አስተዋጽኦዎችን አበርክቷል። በዋናነትም የእንቁላልና የወተት ምርት በከፍተኛ መጠን ጨምሯል። በዚህም በእነዚህ ምርቶች ላይ የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋትም ተችሏል።

አምራቹም አዲስና ተጨማሪ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚያመርትበትን ሥርዓት እንዲከተል አድርጎታል። ይህም አምራቹ ብዙ በማምረት ብዙ ገቢ እንዲያገኝ ከማድረጉም ባሻገር ሁሉም የተመጣጠነ ምግብ ተጠቃሚ እንዲሆን የመርሃ-ግብሩ መጀመር ወሳኝ ሚና ተጫውታል።

አቅርቦት ሲጨምር የሥነ-ምግብ ዋስትናም በዚያው ልክ እንደሚጨምር የሚያስረዱት ዶክተር ታደለ፤ «የሌማት ቱሩፋት ሥራዎች የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የሥነ-ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥንም ጭምር የሚያመጡ ናቸው» በማለት ይናገራሉ። መርሃ-ግብሩን የተገበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለገበያ ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውም ጭምር ምርቱን እንዲጠቀሙ ፣ አጠቃላይ የምግብ ሥርዓታቸውንም እንዲያስተካክሉ ማድረጉን ያስረዳሉ። ምርት በብዛት እንደሚገባ ጠቅሰው፣ ሸማቹም ጥራት ያለውን ምርት መርጦ እንዲሸምት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል ይላሉ።

ዶክተር ታደለ እንደሚሉት፤ ቀደም ሲል አርሶአአደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነቱን የማሳደግ ባህላቸው ኋላቀር ነው። በተለይ በእንስሳት እርባታ ረገድ የተሻሻሉ ዝርያዎች ማቅረብ ባለመቻሉ አምራቹ ምርታማነቱ ከእጅ ወደ አፍ በሚባል ደረጃ ነበር። አምራቹ ለገበያ የሚያቀርበው ቀርቶ፣ ለራሱም የሚጎርሰው አጥቶ ርዳታ ጠባቂ ሆኖ ቆይቷል።

ዶክተር ታደለ ከሌማት ቱሩፋቱ ጋር ተያይዞ ምእራብ ሸዋ አድአ በርጋ ላይ በተቋቋመው ማእከል የተሻሻሉ እንስሳት ዝርያዎች እጥረት እየተፈታ ነው ይላሉ። የግብዓት እጥረቶችንም መርሃ ግብሩ መቅረፍ መጀመሩ ምርታማነት ላይ በጎ ተፅዕኖ አምጥቷል፤ ለሸማቹ የሚደረገው የምርት አቅርቦትም በእጅጉ ጨምሯል ሲሉ ያብራራሉ።

አርሶአደሩ ምርታማ ቢሆንም፣ ምርቱን ለገበያ የሚያቀርብበት ሥርዓት ካለመዘመኑ ጋር ተያይዞ የሚገባውን ያህል ተጠቃሚ መሆን አልቻለም፤ በተለይ የከተማው ሸማች የሚፈልገውን ምርት በመጠንም ሆነ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማግኘት ሲቸገር ይስተዋላል።

በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች አምራችና ሸማቹን በቀጥታ የሚያገናኝ ድልድይ ባለመኖሩ የግብርና ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት እንዲሁም ሰፊ የመረጃ ክፍተት እንደሚታይበት ይነገራል። ይልቁንም የገበያ ሰንሰለቱ ረጅምና ውስብስብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚጠቀመው ደላላ እንደሆነም ይጠቀሳል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አርሶአደሩ በየአካባቢው የምርት አይነትና መጠን ፍላጎት ልክ አለማምረቱ በሚገባ ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጎታል። አሁን ባለው የገበያ ሥርዓት ዘመኑን የማይዋጅ አሠራር መንሰራፋቱ ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረም ይገለጻል።

ምቹ የመሠረተ ልማት ባለመኖሩ ምርቱ ተጠቃሚው ዘንድ ሳይደርስ ለብልሽት የሚዳረግበት፤ በተለይ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የወተት ምርቶች ማቀዝቀዣ ባላቸው ተሽከርካሪዎች የማይጓጓዙበት ሁኔታ መኖሩን ዶክተር ታደለ ያመለክታሉ። ይህ ደግሞ አርሶ አደሩንም ሆነ ተጠቃሚዎችን እንደሚጎዳና መርሃ ግብሩ ይዞ ከተነሳው ሃሳብ ጋርም እንደሚጣረስ ይጠቁማሉ፤ በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል የሚል እምነት እንዳላቸው ይገልጻሉ።

የአሁኑ የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የግብርና ቢሮ ሃላፊና የቀድሞው የህብረት ሥራ ኤጀንሲ /የአሁኑ ኮሚሽን/ ዋና ዳይሬክተርም የነበሩት አቶ ኡስማን የሌማት ትሩፋት ድምር ውጤትን ተከትሎ አዳዲስ ፍላጎቶች መፈጠራቸውን ይጠቅሳሉ፤ ምርት በስፋት መመረቱን ተከትሎ የገበያ ትስስሩም በዛው ልክ መስፋት ያለበት መሆኑ በሁሉም ልማቱ በተተገበረባቸው አካባቢዎች ያሉ አምራቾች ፍላጎት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። በዚህ ረገድ መንግሥት የገበያ ትስስር ለመፍጠርም ሆነ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥረት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፤ ፍላጎቱ ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ደረጃና ጊዜ ምላሽ ለመስጠት አዳጋች ነው ብለዋል።

«አሁን እየመጣ ያለው ልማት ሰፊና አስተማማኝ ገበያ ይፈልጋል» የሚሉት አቶ ኡስማን፤ ምርቱ አስተማማኝ ገበያ ካላገኘ አጠቃላይ ልማቱን ሊያንገራግጨው ይችላል የሚል ስጋትም አላቸው። በዋናነትም በዶሮና እንቁላል ገበያ ላይ የሚስተዋለው ችግር አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሻም ያስገነዝባሉ። «የዶሮ መኖ በጣም ውድ በሆነበት ሁኔታ በርካታ አምራቾች ካመረቱ በኋላ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ገበያ ልንፈጥርላቸው ካልቻልን የሚመጣው ኪሳራ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ሲሉም ጠቅሰው፣ ጉዳቱ አምራቹ ላይ ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ጭምር ሊሆን እንደሚችል ያብራራሉ።

ዶክተር ታደለ፤ አግሮ ኢንዱስትሪዎች ያለመስፋፋታቸው፤ ያሉትም ቢሆኑ በሙሉ አቅማቸው እየሠሩ አለመሆናቸው የአርሶአደሩን ምርት በሚገባው ልክ እየተረከቡ አይደለም የሚል እምነት አላቸው። ይህም በተለይ በጥሬ ወተት ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ ፈጥሯል ይላሉ። በበየነ-መረብ የሚደረግ የገበያ ልውውጥ ያለመኖሩ አምራቹ ምርቱን የሚያስተዋውቅበት መንገድ እንደሌለም ተናግረዋል።

በዚህ ረገድ መሠራት ባለበት ላይም ዶክተር ታደለ ሲያብራሩ የመጀመሪያው ሥራ ሊሆን የሚገባው አርሶአደሩን በማህበር ማደራጀት መሆኑን ገልጸዋል። ይህም አርሶ አደሮቹ ምርቶቻቸውን ወደ አንድ ማዕከል በማምጣት ለትራንስፖርት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ምርቱም በተቀናጀና በተሳለጠ መንገድ እንዲሸጡ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤ ይህም ወጪና ድካምን ይቀንሳል፤ የግብይት ቅልጥፍናን ይጨምራል» ሲሉም ያብራራሉ። የምርት ብልሽት መጠን እንደሚቀንስም ያስረዳሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ለመፍጠርም በግብርና ውጤቶቹ ላይ የእሴት ሰንሰለት መጨመር ያስፈልጋል። በተለይ እንደ ወተት ያሉ ቶሎ የሚበላሹ ምርቶችን ወደ ቂቤና አይብ በመቀየር የቆይታ ጊዜያቸውን መጨመር ይቻላል። ይህ መሆን ያለበትም ዘመኑ ባፈራቸው ቴክኖሎጂዎች ነው። ለዚህም ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በመተሳሳር ቴክኖሎጂዎቹ በስፋት ለአርሶአደሩ የሚደርሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል።

ዶክተር ታደለ በአምራቹና በሸማች ማኅበራቱ መካከል የኮንትራት ውል ማሰር ያስፈልጋል ባይም ናቸው። በዚህም ሁሉንም የሚጠቅም ሥርዓት መፍጠር ይቻላል። አርሶ አደሩ ከዘመኑ ጋር በመራመድ የላቀ ተጠቃሚ እንዲሆን ገበያ ትስስር የመረጃ መረብ ተዘርግቶለት እንዲጠቀምበት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም የግብይት ወጪን በመቀነስ ሁለቱንም ወገኖች ትርፋማ ያደርጋቸዋል።

ለአምራቾቹ በከተሞች የሰንበት ገበያን የመሰለ ቦታ በመስጠት በሳምንት አንዴና ሁለት ጊዜ ምርታቸውን የሚሸጡበትን፤ ተጠቃሚውም በእቅድ ባነሰ ዋጋ የሚገዛበትን ሁኔታ መፈጠር ይገባል ይላሉ።

እንደ አቶ ኡስማን ማብራሪያ፤ ገበያው ለአምራቹ የሚገባውን ያህል መክፈል ካልቻለ አጠቃላይ ልማቱ ይዳከማል፤ ወደኋላ ይመለሳል። በመሆኑም ዘላቂ የገበያ ትስስር ሥርዓት መፍጠር የዘላቂ ገበያ መነሻ ደግሞ ዘላቂ የምርት አቅርቦት ነው። ዘላቂ ገበያ የሌለው ዘላቂ ምርት ሊያመርት አይችልም። አምራቹ አስተማማኝ ገበያ ካላገኘና የማምረቻ ወጪውን መሸፈን የሚያስችል ተመጣጣኝ ገቢ ካላገኘ ውጤታማ ሊሆን አይችልም።

ዘላቂ ገበያ ለመፍጠር የገበያ አማራጮችን ማስፋት ያስፈልጋል። አምራቹ ከሸማች ሊገናኝ የሚችልባቸውን የምርት ማዕካላትንና ተቋማትን መገንባትም ይጠበቃል። በዋናነትም የሸማች ማህበራት ማጠናከር አለባቸው።

ከዚህ ጋር በተያያዘም በሩቅ ምስራቅ ሀገራትና የአውሮፓ ሀገሮች አምራቹ በቀጥታ ምርቱን የሚያስረክባቸው የሸማች ማህበራት ጠንካራ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ እነዚህ ሀገሮች በዚህ የየሀገራቸውን ሕዝቦች ፍላጎት ከማሟላት አልፈው ወደ ኢንዱስትሪ ያደጉበት፤ እሴት ጨምረው ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ምንጭ የሆኑበትን ስኬትም ጠቅሰዋል።

«የእኛ ሀገር የገበያ ሥርዓቱ ጤንነት የጎደለው ነው» የሚሉት አቶ ኡስማን፤ «አምራች፤ ሸማችም ሆነ አቀነባባሪ ለገበያው በጣም ወሳኝ አካላት ናቸው። በሶስቱ አካላት መካከል ጤናማና ፍትሐዊ የሆነ ግኑኝነት ያስፈልጋል፤ በአንዱ ድጋፍ ሌላኛው አካል ብቻ የሚጠበቀምበት ሳይሆን አንዱ ለሌላው መኖር ዋስትና መሆኑን ማመን አለበት» ይላሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ እነዚህ አካላት በመተማመን በመተሳሰብ በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ አርሶአደሩ በብዙ ልፋት ባመረተው ምርት እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሚዛናዊ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

«የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ምርታማነቱ ቢጨምረም፣ ከሚፈለገው አንፃር አሁንም ብዙ መሥራት ያስፈልጋል» የሚሉት ዶክተር ታደለ፣ ምርቱን በሚገባ ወደ ተጠቃሚው ማድረስ ላይ ክፍተት እንዳለ ይገልጻሉ። አሁን ምርቱ ተትረፍርፎ ያን ያህል ለገበያ ውድቀት ይዳርጋል የሚል ስጋት ባይኖራቸውም ቅልጥፍና የሚጎለው የገበያ ሰንሰለት በዚሁ ከቀጠለ አምራቹ ተጠቃሚ እንደማይሆን፣ አልፎም ተርፎ ተስፋ እንደሚቆርጥ፤ ማምረቱን እንደሚቀንስ ፤ ከገበያ ውጭም የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል፣ መርሃ ግብሩም የታሰበውን ላያሳካ ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ጠቁመዋል።

በዶክተር ታደለ ሃሳብ የሚስማሙት አቶ ኡስማን፤ እንደሸማቹ ሁሉ አርሶአደሩም ተደራጅቶ ጥቅሙን የሚያስከብርበት ሁኔታ መፈጠር አለበት ይላሉ። በማህበር ሆኖ ያመረተውን በቀላሉና በአንድ ቦታ በመሰብሰብ ፤ በተደራጀ መንገድ ገበያና ኢንዱስትሪ ይልካል፤ ይህ ሲሆን የገበያ ሥርዓቱ ይታከማል ብለዋል።

ይህንን ማድረግ ካልተቻለ ግን በተለይ የእንቁላልና ወተት ምርት ቀጣይነት ስጋት ውስጥ ይወድቃል። ከውጭ የሚመጡ የግብርና ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የተያዘውን ትልምም ለማሳካት አዳጋች ይሆናል ይላሉ። አሁን የሚታየውን ምርታማነት ማዝለቅ ካስፈለገ የገበያውን አስተማማኝነት ማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው አስገንዝበዋል።

አዲስ ዘመን | ሰኞ ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ‹‹ጆርናል ለችግር ፈቺ ጥናታዊ ሥራዎች ፋይዳው የጎላ ነው››

*-ዶ/ር ሠራዊት ሀንዲሶ*

**ግርማ መንግሥቴ**

ጆርናል የህትመት ውጤት ነው። እንደማንኛውም መረጃ ማቀበያ መሣሪያዎች ጆርናልም መረጃ አቀባይ፤ ሰጪ መሣሪያ ነው። እንደማንኛውም ሰው ሰራሽ ምርት ጆርናልና ኮንቴንቱ (ይዘቱ)ም ሰው ሰራሽ፣ በሰው ልጅ የሚመረቱ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት፤ ከሰው መርጦ ለሹመት እንደሚባለው፣ ጆርናልም ስክሪፕቶ ያለው ሁሉ ጣቱን የሚቀስርበት የሰነፎች መናኸሪያ ሳይሆን ለበቃ አእምሮ፣ ለላቁ ባለሙያዎች፣ ሊቃውንት የተመደበ የሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ሥፍራ ነው።

ጆርናል፣ እንደ ዛሬው እንግዳችን ዶ/ር ሠራዊት አተያይ ችግር ፈቺ፣ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብ፣ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎች፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ ትምህርት ጥያቄዎች የሚነሱበትና ለሰው ልጅ ጥያቄ ተገቢው መልስ የሚሰጥበት፤ "ሳይንሳዊ የምርምር ጆርናል" ብለን የምንጠራው ሲሆን፤ ለሌላው ዓለም ሁሉ የሚተርፉ ሃሳቦች የሚስተናገዱበት የምርምር መጽሔት ወይም ሰነድ ነው።

ጆርናል ከተለያዩና አዳዲስ አተያዮች፣ ንድፈ-ሃሳቦችና ሥነ-ዘዴዎች፣ አኳያ ለተቃኙ የፈጠራ ሃሳቦች እና/ወይም የምርምር ሥራዎች (innovative researches) ቅድሚያና ልዩ ትኩረትን የሚሰጥ ሲሆን፤ ተመራማሪዎቹም ከመጽሔቱ ባልተናነሰ ለእነዚህ ጉዳዮች ልዩ ትኩረትን መስጠት ይጠበቅባቸዋል የሚለው ሚዛን የደፋ አስተያየት ነው።

ከዚህ አኳያ የሀገራችንን ጆርናሎች የተመለከትን እንደ ሆነ የእስካሁኖቹ በተቃራኒው ሆነው ነው የምናገኛቸው።

በትምህርት ሚኒስቴር የምርምርና ስርፀት ዴስክ ሃላፊ የሆኑት ዶ/ር ሠራዊት ሀንዲሶ እንደሚሉት ምንም እንኳን ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን "የምርምር መጽሔት" በሚል ስያሜ የሚታወቁ ጆርናሎች ይዘጋጁ የነበሩ መሆናቸውን የሚያሳዩ ሰነዶች ቢኖሩም፤ በተለይ ባለፉት 20 ዓመታት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መስፋፋት ቢታይም ከተደራሽነትና ተሳትፎ አኳያ ጥሩ ሲሆን፤ ጥራት ላይ ግን ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል። ያ የጥራት ችግርም እስከ ጆርናሎቹ ጥራት መጉደል ድረስ መጥቷል። በመሆኑም ጆርናሎቹ ከጥራት፣ ሳይንሳዊነት (ከይዘትም ሆነ አቀራረብ) የጎደላቸው፣ የማህበረሰቡን ችግሮች ከመፍታት፣ ከተወዳዳሪነት አንፃር ሲታዩ ከፍተኛ ችግር ያለባቸው ሆነው ነው የሚገኙት። ያ ማለት ደግሞ ለእውቀት የምናደርገውን አስተዋፅኦ አናሳ ያደርገዋል። እውቀት የማምረት አቅማችንን ያወርደዋል ማለት ነው። የተመረተውንም ካየነው ጥራት ያለው አይደለም። ከመደርደሪያ ላይ ወርዶ ሊነበብ የሚችል አይደለም።

ሃላፊው እንደሚሉት በእንጭጭ ደረጃ ላይ የሚገኙት ጆርናሎቻችን በተለይ ዓለም አቀፍ አተያይ ላይ ከፍተኛ ችግር ነው ያለባቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ጥናት ይዘው የሚቀርቡ አይደሉም። በመሆኑም፣ ተቀባይነታቸው እስከዚህም ነው። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ደረጃ ያወጣል፤ ያን ጊዜ የኛዎቹ ከተወዳዳሪነት ውጪ ነው የሚሆኑት። በመሆኑም በዓለም አቀፍ የፈጠራ ሥራዎች መጠቆሚያ (Global Innovation Index) ላይ ስር ሆነን እንገኛለን ማለት ነው።

ትምህርት ሚኒስቴር ጥራትን ለማስበቅ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መመሪያ አውጥቶ በመሥራቱ በተወሰነ ደረጃ ለውጥ እየታየ፤ መሻሻል እየመጣ ይገኛል ያሉት ዶክተሩ፣ በአሁኑ ሰዓትም 8 ጆርናሎች ዓለም አቀፍ ደረጃን ተቀላቅለው በ "International Scientific Indexing (ISI)" ዳታ ቤዝ ውስጥ እንደሚገኙም ተናግረዋል። ይህ ማለት ግን እነዚህ ጆርናሎች ጥራት፣ ተከታታይነት፣ ወቅታዊነታቸውን እየጠበቁ ካልሄዱ ከዛ ደረጃ እንደሚወጡም መታወቅ ያለበት መሆኑን አስረድተዋል።

መመዘናቸውን የሚናገሩት ዶ/ር ሠራዊት አንድ እውቅና ለሶስት ዓመት እንደሚቆይና በአራተኛው ለዳግም እውቅና እንደገና እንደሚወዳደር፤ ለዚህም መረጃዎቹን ሁሉ ይዞ እንደሚቀርብ ይናገራሉ። እውቅናው ሶስት ዓመት እንዲሆን የተደረገበትን ምክንያትም "ለማበረታታት" መሆኑንና ሌላው ዓለም ግን በወራት ሁሉ እንደ ሆነ ያስረዳሉ።

ትምህርት ሚኒስቴር በጆርናሎች ብዛት (አንድ ተቋም 10 እና 15 ጆርናሎች ስላሳተመ፤ ወይም በተለያዩ የትምህርት አይነቶች የተበጣጠሰና የተዋቀረ ጆርናል) ችግር ይፈታል ብሎ አያምንም። ትምህርት ሚኒስቴር ጥራታቸውን የጠበቁ፣ ዓለም አቀፍ እይታ ያላቸው፤ ሳይንሳዊ የሆኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆን ሊመረጡ የሚችሉ ጆርናሎችን ነው የሚያበረታታው። በመሆኑም፣ ከማብዛት ይልቅ ባሉትና በተወሰኑት ላይ በሚገባ መሥራትን ያበረታታልም ነው የሚሉት ሃላፊው።

ጆርናሎች የተለያዩ አካላትን ሊያስተናግዱ እንደሚችሉና ሊሆንም እንደሚገባ መመሪያው "ዳይቨርሲቲ" ብሎ ያስቀመጠ መሆኑን የሚናገሩት ዶ/ር ሠራዊት ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያለ ተመራማሪ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጆርናል ላይ ሊያሳትም እንደሚችል፤ የግድ እሱ በሚያጠናው መስክ እዛ ጆርናል መኖር እንደሌለበት ይናገራሉ።

ወጣት ምሁራንን በተመለከተም ጆርናል በከፍተኛ ደረጃ ጠቃሚ መሆኑን የተናገሩት ዶ/ር ሠራዊት ወጣት ምሁራን፣ እጩ ዶክተሮች ጥናቶቻቸውን ታዋቂ ጆርናሎች (ከጥራት፣ ተወዳዳሪነት፣ ተደራሽነት አኳያ) ላይ ቢያሳትሙ እነሱም፣ ሀገርም፣ ዓለምም ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይናገራሉ። ተቋማቸውም ይህንን እንደሚያበረታታ አስታውቀዋል።

ይህንን መሠረት ባደረገ መልኩ በሀገራችን እውቅናን አግኝተው ለህትመት እየበቁ ያሉና በቅተው የነበሩ በርካቶች ሲሆኑ፤ በ2016 እውቅና ከተሰጣቸው 17 የምርምር ጆርናሎች መካከል በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የሚታተመው፣ የጎንደር ዩኒቨርሲቲው EJBME (Ethiopian Journal of Business Management and Economics) ይገኝበታል፤ በአጠቃላይም ዩኒቨርሲቲው አራት ጆርናሎች አሉት።

"ከእነዚህ ጆርናሎች በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው በሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ Disability, CBR and Inclusive Development Journal (DCIDJ) እና Ethiopian Journal of Natural and Computational Sciences (EJNCS) የሚባሉ የምርምር ጆርናሎችን በማሳተም ለእውቀት ሽግግር፣ ለሳይንሳዊ ምርምሮች ስርጭት እና ለማህበረሰብ ሁለንተናዊ ለውጥ አይነተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።" የሚለውንና ስለዩኒቨርሲቲው የተነገረን እውነት እዚሁ ላይ ጠቅሶ ማለፍ ተገቢ ይሆናል።

ይኸው ዩኒቨርሲቲ ለምርምር ጆርናል ለየት ያለ ትኩረትን የሚሰጥ ሲሆን፣ የዚህ ማሳያው ደግሞ በየአመቱ የምርምር ሳምንትን ማክበሩና በዩኒቨርሲቲው ጆርናል ህትመቶች ላይ ውይይት ማድረጉ፤ እንዲሁም፣ "ናይል የኢትዮጵያ ህዳሴ ጆርናል" ን በመሳሰሉት ላይ መነጋገሩ ነው። ይህ አይነቱ የምርምር ባህል በሌሎች የትምህርት ተቋማት ይኑር ወይም አይኑር ለጊዜው ማወቅ ባይቻልም፣ ይኖራል ብለን በማሰብ ልናልፈው እንችላለን።

የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲዎቹ "Hawassa Journal of Law"፣ Ethiopian Journal of Education Studies እና "Journal of Science and Development" ጆርናሎች የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ የግምገማ መስፈርት በማሟላት እውቅናውን ያገኙ መሆናቸውን ሚኒስቴሩ አስታውቆ የነበረ መሆኑም የሚታወስ ነው።

የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሚያሳትመውና ትኩረቱን በፋይናንስ፣ ቢዝነስ፣ ኢኮኖሚክስ እና ልማት መስኮች ላይ ያደረገው፣ የፖሊሲ እና ችግር ፈቺ ምርምሮች የሚቀርቡበት ነው የተባለው African Journal of Economics and Business Research ጆርናል በአፍሪካ ጆርናሎች ኦንላይን (AJOL) ድረ-ገጽ (https://www.ajol.info/index.php/ajebr) ላይ መካተቱን ዩኒቨርሲቲው ከለቀቃቸው መረጃዎች ማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ይህም የጆርናሉን ተደራሽነትንና ተነባቢነትን የበለጠ እንዲጨምር እንዳደረገው ከዩኒቨርሲቲው የወጡ መረጃዎች ይገልፃሉ።

በሦስተኛ ዙር ለሶስት ዓመት የሚቆይ ዕውቅና ከተሰጣቸው 15 የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች አንዱ የሆነውና በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የሚዘጋጀው East African Journal of Veterinary and Animal Sciences ጆርናልም አንዱና ተጠቃሽ የሀገራችን ጆርናል ሲሆን፤ የጅማ ዩኒቨርሲቲው፣ በእንግሊዝኛ እና በአፋን ኦሮሞ የሚታተመው Gadaa ጆርናልም ተመሳሳይ ነው።

የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ "በትምህርት ላይ ትኩረት በማድረግ ምርምር ለሚሠሩ ተመራማሪዎች እንዲሁም ለትምህርት ዘርፍ ማህበረሰብ ትልቅ ፋይዳ" ይኖረዋል በሚል እሳቤ መነሻነት "ኮተቤ የትምህርት ጆርናል" (KOTEBE JOURNAL OF EDUCATION, KJE) ያዘጋጀውን የመጀመሪያ ህትመት ማስመረቁን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ብርሃነመስቀል ጠና (ዶ/ር) መግለፃቸው፤ በዚሁ ህትመት "ተቀባይነት ያገኙ ስድስት ጥናታዊ ፅሑፎች መካታቸውን" የጆርናሉ ዋና አርታኢ ሩቂያ ሀሰን (ዶ/ር) መግለፃቸው ይታወቃል።

በሦስተኛው ዙር ዕውቅና ከተሰጣቸው 15 የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች አንዱ የሆነው፣ የዲላ ዩኒቨርሲቲው Ethiopian Journal of Environment and Development EJED፤ ለሦስት ዓመት የሚቆይ ዕውቅናን ከትምህርት ሚኒስቴር ያገኘው፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲው Daagu International Journal of Basic and Applied Research ወዘተ ጆርናሎችም እንዲሁ ተገቢውን ፈተና አልፈው እዚህ የደረሱ፤ ወደ ፊትም እየተሻሻሉ፣ ጥራትና ተወዳዳሪነታቸውን ከፍ እያደረጉ ለታሪካዊነት ይበቃሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው። እንደ ዶክተር ሠራዊት አስተያየትም ይህ ይሆን ዘንድ ነው ምዘናና እውቅናው በየሶስት ዓመቱ ያስፈለገው።

ለማሳያ ያህል እነዚህን እንጥቀስ እንጂ እንደ ሀገር ካየነው ጉዳዩ ደረት የሚያስነፋ አይደለም።

በአፍሪካ ደረጃ 7ኛ መሆናችእንን የገለፁት ዶክተር ሠራዊት እንዳጫወቱን ከሆነ የሀገራችን ጆርናሎች ከጥራትና ተወዳዳሪነት አኳያ ይቀራቸዋል። ትምህርት ሚኒስቴርም ጆርናልን በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ጥራትን ማስጠበቅ እንደ መሆኑ መጠን በጥራት ላይ ምንም አይነት ድርድር የለም።

ዶክተር ሠራዊት እንደሚሉት ከሆነ በእውቅናውም ሆነ የምርምር ሥራዎች ሲገመገሙ የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል። ማንም ገምጋሚ ወይም ፈታሽ እሱ የተመረቀበትን ተቋም አያይም። ለጆርናሉ ጥራት ትኩረቱ እዛ ድረስ ሁሉ ይሄዳል።

በፍተሻና እውቅና አሰጣጥ መመሪያ (Amended Guideline for Evaluation of Journals Published in Ethiopia No.: Research 01/2019) መሠረት ለሀገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ለምርምር ተቋማት እና ሙያ ማህበራት ጆርናል የማሳተምና ማስተዳደር ፍቃድ የሚሰጠው፣ በኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር የምርምር እና ስርጸት ዴስክ ኃላፊ ዶ/ር ሠራዊት ሀንዲሶ እንዳሉት ጆርናል ከተመራማሪው በርካታ ቁም ነገሮችን የሚሻ ሲሆን፤ ከሙያና ሥነምግባር አኳያም ኢዲቶሪያል ፖሊሲ፣ ዋና አዘጋጅ፣ መምሪያ (Guideline)፤ አማካሪ ቦርድ፣ እና ሌሎችም በሃላፊነት ይመሩታል። ፈቃድና እውቅና ሲሰጥም እነዚህ ግዴታዎች ናቸው።

ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ የሚታተሙ የምርምር ጆርናሎችን ጥራት ለማሳደግ በማሰብ በዘረጋው የምዘና እና እውቅና አሠራር ሥርዓት መሠረት የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናል አርታኢዎች እና አሳታሚዎች የምንተፋና ዘረፋ (Plagiarism) ችግር እንዳይከሰትና "ጆርናል" የተባለውን ከጨዋታ ውጪ እንዳያደርገው ልዩ ትኩረት በመስጠትና ቅድመ ፍተሻ በማድረግ የምርምር ጆርናል ጥራትን እንዲያስጠብቁ እንደሚያሳስብ ማስታወቁ ይታወቃል። ይህም ለጆርናሎቹ ጥራት የራሱ የሆነ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለውና ባለ ጆርናል ተቋማትም በዚሁ መሠረት ይሠራሉ ተብሎ ይታሰባል።

ዶ/ር ሠራዊት በዴስክ ሃላፊነትና በየምርምር ማበልፀግ ጉድኝት ሥራ አስፈፃሚ ተወካይነት የሚሠሩበት ዘርፍ "በርካታ በሀገር ውስጥ የሚታተሙ የምርምር ጆርናሎች ጽሑፎች (Manuscripts) የምንተፋና ዘረፋ (Plagiarism) መጠናቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ከሚሰጠው ነጥብ በላይ መሆኑን በዚህ ዓመት ባደረገው የፍተሻ ሥራ" ማረጋገጡን አስታውቆ እንደነበር ይታወሳል። ይህ ዳግም እንዳይከሰት ምን እየተሠራ እንደሆነ ጠይቀናቸው እያንዳንዱ ጆርናል በየሶስት ዓመቱ ለፍተሻና ምዘና እንደሚቀርብ፤ ስታንዳርዱን ካላሟላና ወርዶ ከተገኘ እንደሚነጠቅ ነግረውናል።

"ከመጋቢት 30/2016 ጀምሮ የ Plagiarism መጠኑ ከ30% በላይ የሆነ የምርምር ጆርናል ለፍተሻ ብቁ የማይሆንና ዕውቅና የማይሰጠው መሆኑ" ንም በቅርቡ ተቋሙ ይፋ ካደረጋቸው ማስታወቂያዎች ተገንዝበናል።

እንደ ምርምርና ስርፀት ዴስክ ሃላፊው ዶ/ር ሠራዊት ሀንዲሶ ገለፃ እኛ ሀገር ያሉ ጆርናሎች የተወሰኑ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃን የያዙና የታወቁ የመኖራቸውን ያህል ተከታታያይነት የሌላቸው፣ የሚቆራረጡ፣ ሳይንሳዊነት የሚጎድላቸው ብዙ አሉ። እነዚህና ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች ለአቅመ ጆርናልነት የማያበቁ ሲሆኑ፤ እውቅናን ያገኙ እንኳን ቢሆን የተሰጠውን እውቅና የሚያስነጥቁ ናቸው።

በመጨረሻ የሚሉት ካለ ያልናቸው ዶ/ር ሠራዊት፣ እውቀት የዓለም ነው። የሰው ልጅ ሁሉ ነው። በአንድ ቦታ የተወሰነ አይደለም። ቅብብሎሽ ነው። ሳይንስ ደግሞ አንዱ ለሰው ልጅ የተሰጠ ትልቁ እድል ነው። በመሆኑም ይህንን እድል ተጠቅመን እውቀትን ተደራሽ ማድረግ ይገባናል። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ስፍራ ጆርናል ነው። በእነ ስኮፐስ ዳታ ውስጥ ከ40 እስከ 50ሺህ ጆርናሎች አሉ። እዛ ውስጥ መግባት ይገባናል። እዛ ከገባን እንነበባለን። ለዓለም ሁሉ እንተርፋለን። በተለይ ወጣት ምሁራኖቻችን ከደከሙ አይቀር በሚገባ ሠርተው፣ በተዘጋጀ ሥርዓት ውስጥ አልፈውና ተወዳዳሪ ሆነው ሊታዩ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ተገቢው መንገድ ታዋቂ ጆርናል ላይ ሥራዎችን ማሳተም ነው። ትምህርት ሚኒስቴር ይህንን ያበረታታል። ሀገራችንን፣ እራሳችንንም፤ እንዲሁም ሌላውን ዓለም ጭምር እንድንጠቅምና የምርምር ሥራችንን እንድናዘምን በጋራ እንሥራ በማለት መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።



ፎቶ- ዳኜ አበራ፤

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



ፎቶ፡- በረሀን ታደሰ

# "የቤኒሻንጉል ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል አስተሳሰብና ማንነትን ያዳበረው ገና አሁን ነው"

- አቶ አሻድሊ ሀሰን

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርእሰ መስተዳድር

ግርማ መንግሥቴ

ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ከታዳጊ ክልሎች ውስጥ አንዱ ነው። የማእድናት ባለፀጋ ከሆኑትም ቀዳሚው ሲሆን፤ ፀጋዎቹን ወደ ሀብት ካልቀየሩት አካባቢ እንደ አንዱ የሚታይ ነው፡፡ በእስከ ዛሬው የሀገሪቱ ተጠቃሚነትና የመልማት ታሪክ ተግፍቶ የቆየ ክልል ሲሆን፣ በተለይም ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ከባለቤትነትና ተሳታፊነት እንዲሁም ውሳኔ ሰጪነት መድረክ በመራቅ በ "አጋር ድርጅት" ነት የቆየ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

በክልሉና ሕዝቡ ላይ የተፈፀመ ፖለቲካዊ ግፍ መሆኑ በሚመለከታቸው ሁሉ የሚነገርለት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ ከአየር ንብረትና ውሃ ሀብት ጀምሮ ያልታደለው ነገር የለም። በሰው ሀብት በኩል የወጣት ምድር ሲሆን፣ ከልማት አኳያም መልማት የማይችል ቦታ የሌለው ከመሆኑ ባሻገር ያልለማውና እስከ ዛሬ ያለጥቅም የኖረውና እስካሁንም ድረስ "ኑ ብሉኝ፣ ኑ ተጠቀሙብኝ" የሚለው ስፍራ ይበልጣል።

ዛሬ ግን ቀን ተለውጧል፡፡ ክልሉ ወደ ልማት ሀዲድ ውስጥ በመግባት እየገሰገሰ ይገኛል። ክልሉ የማእድንና ግብርናው ዘርፎች በቆሰቆሱት ኢኮኖሚ ሞቅ ደመቅ እያለ መሆኑ በግልፅ ይታያል። በተመቻቸ መልክአምድሩ ሳቢያ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በእቅፉ ያስገባ የወደፊት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እምብርት መሆኑም ከወዲሁ እየተስተጋባለት ያለ የሀገሪቱ አካል ነው።

ክልሉ የተከሰተውን የሠላም እጦት፣ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ሁሉ ወደ አንፃራዊ ሠላም በመመለስ ለውጥና ብልፅግናን የማምጣት ጉዞውን እንደተያያዘውም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አሻድሊ ሀሰን ይናገራሉ። አዲስ ዘመንም ከእርሳቸው ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡

**አዲስ ዘመን:- በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮች እየተመዘኑ ያሉት ሀገሪቱ ውስጥ ከተከሰተው ለውጥ አኳያ ነውና፤ ከለውጡ በፊትና በኋላ ያለውን አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ባጭሩ ቢገልፁልን።**

**አቶ አሻድሊ:-** ባለፉት ስድስት ዓመታት ውስጥ በክልላችን የተመዘገበው ትርጉም ያለው ለውጥ ነው፡፡ ከኢህአዴግ በፊት በነበሩ የአስተዳደር ሥርዓቶች የተረሱ አካባቢዎች የነበሩ ሲሆን፣ አንዱም ይህ የእኛ ክልል ነው። ከመንግሥት የራቀ አካባቢና ሕዝብ ነበር። ሩቅ ነው በሚል ብቻ፣ ኋላ ቀር ነው ከሚል የተሳሳተ እሳቤ በመነሳት ከሀገሪቱ ጥቅም ተገልሎ የኖረ ክልል ነው። ሕዝቡም በባህላዊ አስተሳሰብና አሠራር ውስጥ እንዲቆይ የተደረገ ሕዝብ ነው።

ይህንን እቀይራለሁ ብሎ በ1983 ዓ.ም ወደ ሥልጣን የመጣው የኢህአዴግ መንግሥት ተግባሩ ሁሉ የይስሙላ ነበር። ከእነ ጭራሹ እኛን ከሀገር ባለቤትነት ወደ ዳር በመግፋት "አጋር ድርጅት" በሚል ሰየመን። እስከለውጡም ድረስ የነበርነው በአጋር ድርጅትነት ነው። የነበረው በሕዝብ ላይ የተቀለደበት ሁኔታ ነበር። ሕዝቡ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያ ላይ እንዲወስን አልተደረገም፤ አልተፈቀደለትም ነበር።

ሕዝቡ ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተጋለጠበት ሁኔታ ነበር። ፌዴራል ላይ ሆነው ሕዝቡንና አካባቢውን በእጅ አዙር የሚያስተዳድሩ ሰዎች ነበሩ፡፡ መሬት እንኳን ሳይቀር ወደ ላይ ተስቦ በተወሱ ባለሥልጣናት አማካኝነት ለባለሀብት ተብዬዎች የሚሸነሸንበት ሁኔታ ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢንቨስተሮች የተባሉ ሰዎች የወሰዱትም ለዚያ ነበር፡፡ መሬት ተነጥቆ ካርታቸው እንዲመክን የተደረገውና ለአንዳንዶቹም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው የነበረው ለዚያ ነበር። ክልሉንና ሕዝቡን በአጋር ስም አግልሎ ሲካሄድ የነበረው ልማት ሳይሆን ዘረፋ ነበር።

ክልሉ ራሱን ማስተዳደር አይችልም በሚል ድምዳሜ በራሱ ጉዳይ ነጻ ሆኖ አይሠራም ነበር፡፡ በትእዛዝ ለእነ እከሌ፣ ለእነ እከሊት መሬት ስጥ እየተባለ መሬት ሲሰጥና ሲሸነሸን የነበረው በሞግዚትነት ነበር። ሲኖር የነበረው አቅም ለሌለው ሁሉ መሬት እየተሰጠው፤ ገንዘብ የሌለው ሁሉ ገንዘብ ከባንክ እየወሰደ ምንም ሳይሰራበትና ሳያለማበት ነው። ይህ በበኩሉ በአካባቢው እድገት ላይ ተፅእኖ ፈጥሯል። ክልሉን ወደ ኋላ አስቀርቷል። እንደ ሌሎች ክልሎች እንዳይለማ አድርጎታል። ከለውጡ በኋላ ግን ወደ ላይ ተስቦ የተወሰደው መሬትና የመሬት ጉዳይ ወደ ክልሉ እንዲመለስ ተደርጎ ለባለሀብቶች በመሰጠቱ ምክንያት በርካታ ባለሀብቶች ወደ ሥራ ገብተዋል። ምርታማም በመሆን ላይ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት ከለውጡ ወዲህ እንደ አንድ የሀገሪቱ አካል በመሆን እየተሳተፍን እንገኛለን። የቤኒሻንጉል ሕዝብ እውነትም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል አስተሳሰብና ማንነትን ያዳበረው ገና አሁን ነው። እራሱን በራሱ በትክክል ማስተዳደር የጀመረው ከለውጥ በኋላ ነው። ኢትዮጵያዊነትን የመፍጠር ሥራ እየተሠራ ያለው አሁን ነው፡፡ የራሱን ሀብት መጠቀምና መልማት የጀመረው ከለውጡ በኋላ ነው። በሕገ መንግሥቱ ላይ ሰፍረው የነበሩትን መብቶች በትክክል መጠቀም የቻልነው ከለውጡ በኋላ ነው። ክልላችን በእነዚሁ ዓመታት ውስጥም ከራሱ አልፎ እንደ ሀገር ለፌዴራል መንግሥት ስኬታማነት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በፊት በሀገር ደረጃ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ አንገኝም፤ አንሳተፍም ነበር። የኖርነው ተገልለን ነው። በሀገር ደረጃ ይደረጉ የነበሩ ውሳኔዎች ይደርሱን የነበረው በተዘዋዋሪ ነበር። ክልሉ ሲመራ የነበረው አማካሪ ምናምን እየተባለ ነበር። ከለውጡ በኋላ ግን ይህ ሁሉ ቀርቶ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት፣ እንደ ፓርቲም በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋል፤ ውሳኔም ይሰጣል። ለውጡ ይህንን ያህል ተጨባጭ ለውጥ ይዞ የመጣው።

እንደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ሕዝብ፣ ለውጡ ትልቅ ስፍራ፣ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ የክልሉ ሕዝብ እውነትም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል አመለካከት እንዲኖረው ያደረገ፤ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ወሳኝ መሆኑን ያረጋገጠበት ለውጥ በመሆኑ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

> **ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው በተለይ የክልሉ መንግሥት ከአጋር ድርጅትነት ወደ ወሳኝና ውሳኔ ሰጪ ድርጅትነት መቀየሩን ተከትሎ ነው**

**አዲስ ዘመን:- ከኢኮኖሚያዊ እድገት አኳያ ያለውንስ እንዴት ይገልፁታል?**

**አቶ አሻድሊ:-** የለውጡ ሃይል ገና ወደ መንግሥታዊ ሃላፊነት ሲመጣ የኢኮኖሚ ፍትሃዊነት እንዲኖር ይፈልግ ነበር። በዚሁ መሠረትም እኩል የማደግ እድል ለሁሉም ክልሎች ሰጥቷል። በዚህ እድል ተጠቅመን እየሠራንና እያለማን፤ ከተረጂነት ወደ አምራችነትም እየተቀየርን እንገኛለን።

እንደሚታወቀው በክልላችን ሊታረስ የሚችል፣ ሊያመርት የሚችል፤ በአጠቃላይ ለእርሻ ምቹ የሆነ ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት አለ። ይህ ማለት በብዙ የአፍሪካ ሀገራት የሌለ መሬትና አቅም ነው። እዚህ ግን በኢትዮጵያ በአንድ ክልል ያለ ሀብት ነው፤ ትልቅ አቅም አለ ማለት ነው። ይህ ወደ ሥራ ቢገባበትና ቢለማ ከክልል፣ ከሀገርም አልፎ ለውጭ ገበያም በመትረፍ የሀገርን ኢኮኖሚ ይጠቅማል ማለት ነው።

ከለውጡ በኋላ ወደዚህ፣ ወደ ማልማቱ ሥራ እየተገባ ነው። አሁን ባለሀብቶች በዘርፉ እየተሰማሩ ይገኛሉ። ለመሥራት የሚያስችላቸውንም ገንዘብ ከባንክ እየወሰዱ ይገኛሉ። እስካሁንም ከ900 ሄክታር መሬት በላይ ወስደዋል። ወደ ሥራም እየገቡ ይገኛሉ። በአሁኑ ሰአት ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት እየለማ ይገኛል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ኢኒሼቲቭ መሠረት ስንዴ ዘርተንባቸው የማናውቃቸውን ቦታዎች በመለየት በተለያዩ አካባቢዎች በማምረት ላይ እንገኛለን። ለአርሶ አደሩ ድሮ ውስን ተደርጎ ይሰጠው የነበረው ግብዓት ከለውጡ በኋላ ተገቢውን፣ የሚፈልገውን ግብዓት እያገኘ ነው።

ከለውጡ በፊት ይህንን የሚያክል አቅም ያለው ክልል ከ700 ሺህ ሄክታር በላይ አምርቶ አያውቅም ነበር። ከለውጡ በኋላ ግን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት በአርሶ አደር ብቻ ለምቷል። ይህ ቀላል ግምት የሚሰጠው ለውጥ አይደለም። በዚህ ከቀጠለ ክልሉ የወደፊቱ የሀገሪቱ የልማት ኮሪደር የመሆን እድሉ ሰፊ ነው።

**አዲስ ዘመን:- በኢንዱስትሪው ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት አሉ? ካሉ ቢገልፁልን።**

**አቶ አሻድሊ:-** በዚህ ዘርፍ አቅሙ እያለ ያልተሠራበት ዘርፍ ነው። ባምቡ ፋብሪካ፣ እምንበረድ እና ሌሎች ከእምነበረድ ጋር የተያያዙ ዘርፎች ወደ ሥራ የተገባባቸውና እየተገባባቸው ያሉ ናቸው። የዱቄትና ሌሎች ፋብሪካዎችም ወደ ሥራ ገብተው በምርት ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ብዙ መሥራት እየተቻለ በሰላም እጦት ምክንያት እንደተፈለገው መሄድ አልተቻለም። በተለያዩ በግብርና እና ሌሎች ዘርፎች ከ900 በላይ ባለሀብቶች ፍቃድ ወስደው ወደ ሥራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ነበሩ። ያልገቡ አሉ። መግባት ሳይችሉ የቀሩት በዚሁ በሰላም ማጣት ችግር ሲሆን፤ አሁን በተፈጠረው አንፃራዊ ሰላም ግን ወደ ሥራ በመግባት ላይ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን:- ክልሉ በማዕድን ሀብትም ይታወቃልና በዛ በኩል ያለውን ገፅታ ቢገልጹልን ?**

**አቶ አሻድሊ:-** ገና በጥናት ያልተደረሰባቸውን ሳይጨምር፣ ክልላችን ከሁሉም በበለጠ በማዕድን ሀብት የበለፀገ ክልል ነው። ይህ ሀብት ከለውጡ በፊት እንዲነካ ሁሉ አይፈልግም ነበር። የፖሊሲ አቅጣጫም ሆነ የሕግ ማእቀፍ ሁሉ አልነበረውም። ዛሬ ያ ሁሉ ቀርቶ የማእድን ሀብቱን መጠቀም ጀምረናል። ለፌዴራልም ገቢ በማስገባት ላይ እንገኛለን።

ለምሳሌ በ2013 ዓ.ም 30 ኩንታል (3000 ኪሎ ግራም)፤ በ2014 ዓ.ም ደግሞ ሁለት ሺህ 300 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሄራዊ ባንክ ገቢ ተደርጓል። ይህ በጥቁር ገበያ በኩል እየሄደ ያለውን ሳይጨምርና በማህበራት በኩል በተደራጁ ወጣቶች አማካይነት ከተሠራው የተላከ ብቻ ነው።

በአሁኑ ሰአት ወጣቶች ተደራጅተው ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን፣ በከፍተኛ ደረጃም ተጠቃሚ እየሆኑ፤ አካባቢያቸውን የማልማት ተግባራት ላይም እየተሳተፉ ይገኛሉ። አሠራራቸውም ከኋላ ቀር አሠራር እንዲላቀቅ እየተደረገ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “የቤኒሻንጉል ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል አስተሳሰብና...

ከገጽ 9 የዞረ

ሲሆን፣ ወደ ዘመናዊ አሠራርና ቴክኖሎጂ አጠቀቃቀም በመሸጋገር ላይ ናቸው።

ወጣቱ ከአህያ ወደ ሞተር፤ ከሞተር ወደ መኪና እየተሸጋገረ ይገኛል። በሶስት ዓመታት ውስጥ ብቻ፣ ከለውጡ በኋላ ከ300 በላይ መኪኖችን የገዙ ወጣቶች ያሉባቸው አካባቢዎች አሉ። በኩምሩህ አካባቢ ብቻ ከ80 በላይ መኪኖች ተገዝተው ሥራ ላይ ናቸው። ሸርቆሌ አካባቢ ከአራትና አምስት ዓመት በፊት አንድ ብስክሌት እንኳን ያልነበረበት ሁኔታ ነበር። ዛሬ ሞተርና መኪና እንደ ልብ ነው። ካማሺ አካባቢ የድንጋይ ከሰል በስፋት እየተመረተ፣ ሀገር ዶላር እያዳነች፤ የአካባቢው ህብረተሰብም በከፍተኛ ደረጃ በመለወጥ ላይ ነው።

በአሁኑ ሰአት በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እንቅስቃሴ ማየት ተችሏል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከሁሉም በላይ በማእድኑ ዘርፍ እየታየ ያለው ሰፊ እንቅስቃሴና እየተገኘ ያለው ውጤት ነው።

ዛሬ፣ እንኳን መኪና ሊገዙ መኪና እንኳን አይተው የማያውቁ አካባቢዎች በዚህ ደረጃና ፍጥነት ባለ መኪና መሆናቸው ሲታይ በክልሉ ከፍተኛ ለውጥ ስለ መኖሩ ተገቢ ማሳያ ነው። አሁንም ከማህበራቱ በዘለለም፣ ወጣቶቻችን ተደራጅተው ከባለሀብቱ ጋር በመሆን በ70/30 (ማሽኖችና የመሳሰሉት ከባለ ሀበቱ) አሠራር እየሠሩ ይገኛሉ። ይህም የማእድን ሀብት አላቂ ከመሆኑ አኳያ ባለ ሀብቱ ብቻ አምርቶ እንዲሄድ ስለማያደርገውና የአካባቢው ማህበረሰብም ተጠቃሚ ስለሚሆን የተሻለ ተጠቃሚነትና ኢኮኖሚያዊ እድገት እየመጣ መሆኑ ግልፅ ነው።

በክልሉ፣ በተለይም በከተሞች ዛሬ ቁጠባ ባህል እየሆነ ነው። በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ባንክ ማስቀመጥ የተለመደ ብቻ ሳይሆን ተገቢነቱን አምኖ የተቀበለ ማህበረሰብ በስፋት ተፈጥሯል። በአካባቢ ልማት እየተሳተፉ ያሉ ወጣቶች ብዙ ናቸው። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ከፌዴራል ጀምሮ ባለው መስተዳድር የአካባቢው የማእድን ሀብት ማህበረሰቡን ሊቀይር የሚችል አቅም ያለው መሆኑ ታምኖበት እየተሠራ በመሆኑ ነው።

በአሁኑ ሰአት እነዚህ ወጣቶች ከተሞች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ጀምረዋል። ካማሽ ዞን ላይ የድንጋይ ከሰል ማምረት ተጀምሯል። የድንጋይ ከሰል ሃይል (ኢነርጂ) ነው፤ አስፈላጊ ብቻም ሳይሆን አዋጭም ነው። እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉ ተግባራት ከለውጡ በኋላ የህብረተሰቡ ሕይወት በከፍተኛ ደረጃ እየተለወጠ ይገኛል። የሰላም እጦት ችግር ባያጋጥመንና ትኩረታችንን ባይወስድብን ኖሮ ከዚህ በተሻለ በመሥራት የትና የት በደረስንም ነበር።

እየተመረተ ባለው እምነበረድ ምክንያት ሰፊና እያደገ የሚሄድ የሥራ እድል ተፈጥሯል። ህብረተሰቡ ሀብት እያፈራ ነው። በሂደት ወደ ኢንዱስትሪውና ግብርናው ዘርፍ እንዲገቡ ነው አቅጣጫ አስቀምጠን እየሠራን ያለነው። በየዞኑና ወረዳዎች ያሉ አካባቢዎች እየለሙ ነው። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው በተለይ የክልሉ መንግሥት ከአጋር ድርጅትነት ወደ ወሳኝና ውሳኔ ሰጪ ድርጅትነት መቀየሩን ተከትሎ ነው። ይህ የህብረተሰቡን ሞራል እጅጉን ገንብቶታል። ተጎድቶ ነበረውን ስሜቱን መልሶ አድኖታል። የሥራ ሞራሉ፤ ሰርቶ የመለወጥና የማደግ ፍላጎቱን ሁሉ ከፍ አግርጎታል። ለውጡ ቀላል አልነበረም፤ አይደለምም።

ሌላው የክልሉ የማእድን ሀብት እጣን ነው። በፊት አንድ ወይም ሁለት ባለ ሀብቶች ብቻ ነበሩ እንደፈለጉ የሚያደርጉት። አሁን ክልሉ በእውነተኛው ራሱን ማስተዳደር ከጀመረ፣ ከለውጡ ወዲህ ግን በርካታ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን፤ አሁን ማህበረሰቡ ተደራጅቶ እየሠራ ይገኛል። ወጣቶች አንድ ኩንታል እጣን 40 ሺህ ብር በመሸጥና ተጠቃሚ መሆን ላይ ናቸው። ይህ ሁሉ የመጣው ከለውጡና የለውጡ ሃይል ሁሉም ክልሎች እኩል የመልማት መብት አላቸው ብሎ ከማመኑ፤ ከሚያፈልቃቸው አዋጭና ጠቃሚ ሃሳቦች፤ እንዲሁም የማይናወጥ ጠንካራ የመበልፀግ አቋም ከመያዙ፤ የክልሉ አመራርም በማእድኑ ዘርፍ በሚገባ ከተሠራ በክልሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ይመጣል ብሎ ከማመኑና በዛው ልክ በመሥራት ላይ በመሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ፣ ያለ ምንም ሞግዚት ራሳችን፣ የፌዴራሉን እቅድ በተንተራሰ መልኩ የራሳችንን አካባቢ በራሳችን እቅድና ፕሮግራም ማልማት ከመቻላችን የመጣ ከፍተኛ ለውጥና እድገት ነው።

**አዲስ ዘመን:- በማህበራዊው ዘርፍስ ያለው ሁኔታ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ አሻድሊ:-** ከትምህርቱ ዘርፍ ለመጀመር ያህል፣ በክልሉ ከለውጡ በኋላ ትምህርት ተስፋፍቷል። ተደራሽነቱም በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። ጥራትን ለማምጣትም እየተሠራ ነው።



በአሁኑ ሰአት በሁሉም አካባቢዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ማእከላዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ እየተገነቡ ነው። በ“ትምህርት ለትውልድ” ሀገራዊ እንቅስቃሴ መሠረትም እየተሠራ ይገኛል። በትምህርት ቤቶች የምገባ ፕሮግራሞች ተጀምረዋል፤ ለውጥም እየታየ ይገኛል። አዳሪ ትምህርት ቤትም በመገንባት ላይ ነው።

ወደ ጤናው ሴክተርም ስንመጣ በተመሳሳይ ሁኔታ ለውጦች አሉ። ከለውጡ በፊት መከላከል ላይ ብቻ ያተኩር የነበረው የህክምና ፖሊሲያችን በአሁኑ ሰአት ከፍተኛ መሻሻልን አምጥቶ መከላከልና ማከም ላይ እየሠራ ይገኛል።

በክልላችን አምስት የመጀመሪያ ደረጃ (ፕራይመሪ) ሆስፒታሎች እየተገነቡ ሲሆን፣ አራቱ ተጠናቅቀዋል። በርካታ ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች ተሠርተዋል፤ ነባሮቹም እየተጠናከሩ ነው። አጎበር በማሰራጨት ወባን ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። ህክምናን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የጤና መድህን ላይ በስፋት እየተሠራና ህብረተሰቡን መቶ በመቶ የጤና መድህን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ለውጥም እየመጣ፣ ውጤትም እየተመዘገበ ይገኛል።

ከቱሪዝም አኳያም የውሃ ሀብት በብዛት ያለን በመሆኑ ወንዞች ላይ እየሠራን ነው። ተራሮች አሉ፤ በእነርሱ ላይም እየሠራንባቸ ነው። በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያም እየተሠሩ ያሉ በርካታ ሥራዎች አሉ። ወደ ፊት ትልቅ ከተማ ይገነባል ተብሎም ይጠበቃል። ቤተመንግሥቶች አሉ፣ እየተጠበቁና ለቱሪዝም ዘርፉ አገልግሎት እንዲውሉ እየተደረጉ ናቸው።

**አዲስ ዘመን:- ከመሠረተ-ልማት አኳያ የተሠሩ ሥራዎች ካሉ ቢገልጹልን፡፡**

**አቶ አሻድሊ:-** በከተማ ውስጥ በአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በጀት የአስፓልት መንገድ እየተሠራ ይገኛል። ከለውጡ በፊት ያለ ጥናት ወደ ግንባታ የተገባበት ስታዲዮም እንደ ገና እንዲጠና ተደርጎ በካፍ ስታንዳርድ መሠረት መልሶ የመገንባቱና ማጠናቀቁ ሥራ በመጀመር ላይ ይገኛል። ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መጽሐፍ (መደመር) በተገኘ የ300 ሚሊዮን ብር ገቢ በከተማችን ውስጥ ዘመናዊ ሙዚየም በመገንባት ላይ ነው። ግሽበትና ካሳ ፈተና ቢሆንብንም እስካሁን የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ያለ ማቋረጥ እየሠራን እንገኛለን። የሰላም መደፍረስ ቢረብሸንም ልማትን አላቆምንም። በርካታ በፌዴራል የተጀመሩና ተቋርጠው የነበሩ የመንገድ ሥራዎች እንዲጀምሩ ለማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን ወዘተ በተመለከተ አስቀድሜ እንደገለፅኩት በስፋት እየተሠሩ ነው።

**አዲስ ዘመን:- በአረንጓዴ ዐሻራ ዙሪያ ምን ያህል ተሠርቷል?**

**አቶ አሻድሊ:-** በአረንጓዴ ዐሻራ ላይ በስፋት እየሠራን እንገኛለን። አረንጓዴ ኢኮኖሚ (ግሪን ኢኮኖሚ) እየገነባን ነው። በዓመት በአማካይ 50 ሚሊዮን ችግኞችን እንተክላለን። የገቢ ምንጭ የሆኑትን፣ እንደነ ማንጎ፣ አቡካዶና የመሳሰሉ አትክልቶችንም እየተከልን ነው። በክልሉ አራት የከተማ አስተዳደሮች አሉ። በሁሉም የማፅዳትና ማስዋብ ሥራዎችን ያለ ማቋረጥ እየሠራን እንገኛለን። በሠራነው ልክም ውጤታማ እየሆንን ነው።

**አዲስ ዘመን:- ሀገራዊ አጀንዳ በሆነው የሌማት ትሩፋት ዘርፍስ የተሠሩ ሥራዎች ይኖሩ ይሆን?**

**አቶ አሻድሊ:-** አዎ! ተጠቃሽ ሥራዎች አሉ። በክልላችን አሶሳ ከተማ ውስጥ ሁሉን አካታች የሆነ ሞዴል ማእከል ተፈጥሯል። የተገነባውም በክልል ፕሬዚዳንት ልዩ ጽሕፈት ቤት ድጋፍና ክትትል ነው፤ አሁንም ድጋፍና ክትትሉ አልተቋረጠም። በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። የዋጋ ግሽበትን ከመከላከልና መቆጣጠር ባሻገር፤ ነዋሪዎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ ነው። ዶሮ፣ እንቁላል፣ ማር፣ አይብ ወዘተ ለገበያ በመቅረብ ላይ ይገኛል። ገበያን የማረጋጋት ሥራ እየተሠራ ይገኛል፤ ለውጥም ተገኝቶበታል። ዘርፉ የግል ባለሀብቶችም እንዲገቡበት እየተደረገና እየተስፋፋ ይገኛል። ሌሎች፣ እስከ ገጠር ወረዳና ቀበሌዎች ድረስ እሱን በሞዴልነት እንዲከተሉትና እነሱም እሱን መሰል ማእከል እንዲገነቡ እየተደረገ ነው። 25 ሺህ የአንድ ቀን ጫጩት መያዝ የሚችል ማእከል (ኢንኪዩቤተር)ም በመገንባት ላይ ነው።

ከሌማት ትሩፋት አንዱ የሆነው የዓሳ ልማትም እየተሠራባቸው ካሉት ተግባራቶቻችን አንዱ ሲሆን፤ በተለይ ከህዳሴው ግድብ ጋር በተያያዘ የዓሳ ልማቱ በጥሩ ሁኔታ እየተሠራበት ይገኛል። ወጣቶች እየተደራጁ በመሥራት ላይ ናቸው። ከፍሪጅ ጀምሮ እስከ እንዴት ፕሮሰስ አድርጎ ለገበያ (ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ) ማቅረብ እስከሚቻልበት ሁኔታ ድረስ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል መሠረተ ልማት እየተካሄደ ነው። በተለይ ከአቅርቦትና ገበያን ከማረጋጋት አኳያ ተስፋ ሰጪ ለውጦች እየታዩ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን:- ወደ ሠላም እና ፀጥታው ዘርፍ እንምጣና የነበሩትን ተግዳሮቶች፤ እንዲሁም፣ አሁን ያለውን ተጨባጭ የሠላም፣ ፀጥታና ደህንነት ሁኔታ ቢገልፁልን?**

**አቶ አሻድሊ:-** ከለውጡ በኋላ ወይም የለውጡን መምጣት ተከትሎ ጥቅሜ ይቀራል በሚል ያኮረፉና ወደ ጦርነት ሳይቀር የገቡ ኃይሎች አሉ። እነዚህ ኃይሎች የፈጠሩት ቀውስ በክልሉ ሰላም እንዲደፈርስ አድርጎ መቆየቱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በተከፈለው ውድ መስዋእትነት አሁን በክልላችን አንፃራዊ ሰላም ሊገኝ ችሏል። በአሁኑ ሰአት በየትኛውም የክልሉ አካባቢዎች መንቀሳቀስ ይቻላል። ትንሽ ችግር ያለው ከአጎራባች ክልሎች ጋር ለመገናኘት አለመቻሉ ነው። በአጎራባች ክልሎች አሁንም የፀረሰላም ኃይሎች እንቅስቃሴ አለ። ከአሶሳ ወደ ባህር ዳር፤ ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ትንሽ ችግር አለ። በአንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎችም እንደዛው። ይህ ደግሞ ሸቀጦችን ከማሳለጥ አኳያ የራሱ የሆነ ችግር ፈጥሯል። ልማት ላይ ሳይቀር እንቅፋት እየሆነ ነው። ሁሉም በእርግጠኝነት በቅርቡ መፍትሄ ያገኛል ብዬ አስባለሁ።

እስካሁን ባለው ሁኔታ የፌዴራል መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋር በቅርበት እየሠራ ነው። ከጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን ጋርም እጅና ጓንት በመሆን ሥንሰራ ነው፡፡

አኩርፈው ጫካ ከገቡት፣ ወደ ጎረቤት ሀገር በመሄድ ተመልሰው ሀገራቸውን ሲወጉ ከነበሩት ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ያልተቋረጠ ውይይት በማድረግና ስምምነት ላይ በመድረስ፤ ወደ ሰላም እንዲመለሱና በልማት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል። በተደረጉት ስምምነቶች ምክንያትም ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት፣ በተለያዩና ባላመኑባቸው ምክንያቶች ወደ ጫካ ገብተው የነበሩት ሲሆኑ፣ ወደ ሰላም ተመልሰው በልማት ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ። ይህ ትልቅ ስኬት ነው ብለን ነው የወሰድነው።

የጠረፍ አካባቢ እንደ መሆኑ መጠን፣ ክልሉ ረዘም ላለ ጊዜ የፀጥታ ችግር ውስጥ መቆየቱ ጎድቶናል። አሁን አንፃራዊ ሰላም አግኝተናል። የመልሶ ግንባታ ሥራዎችንም እየሠራን እንገኛለን። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ብዙ እያገዘን ሲሆን፣ በራሱ ወጪ ትምህርት ቤትና መንገዶችን ሁሉ እስከ መሥራት የዘለቀ ድጋፍን አድርጎልናል። በአማራ በኩል ያለውን ችግር ለመቅረፍም ከክልሉ ሥራ ሃላፊዎች ጋር እየሠራን እንገኛለን። በእነሱም በኩል ድጋፍ አለን።

ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታትም የጋራ (ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ) ጽሕፈት ቤት አቋቁመን እየሠራን እንገኛለን። የጽሕፈት ቤት ህንፃ (ጂ+4) ግንባታውም እየተገባደደ ይገኛል። አብሮና በጋራ በመሥራት ሰላም ማምጣት ይቻላል በሚል እሳቤ የተቋቋመ ጽሕፈት ቤት ነው።

መንግሥት “ያ የኔ፣ ያ ያንተ ችግር ነው” ከመባባል ይልቅ “የአንዱ ችግር የእኔም፣ የሁላችንም ችግር ነው” ብሎ በመውሰድ በጋራ ችግሩን ለመፍታት መሥራት እንደሚገባ አቅጣጫ ይዟል። በዛ መሠረት ነው ይህ በጋራ የመሥራት ነገር የመጣው።

እንደ ሀገር ሁሉ፣ እንደ ክልልም እኛንም ፈተና ውስጥ የከተቱን በርካታ የሰላም እጦት ችግሮች አጋጥመውናል። በተለይ የሰላም ማጣት ከፍተኛ ፈተና ሆኖብን ነበር። ይሁን እንጂ፣ በዛ ውስጥ ሆነን ነው ብልፅግናን ማምጣት የቻልነው። የብልፅግና መንግሥት ችግሮችን፣ ፈተናዎችን ወደ እድሎች መቀየር የሚችል መንግሥት በመሆኑ እነዛን ሁሉ አልፈን ነው እዚህ ውጤት ላይ ለመድረስ የቻልነው።

**አዲስ ዘመን:- የሥራ እድልን በተመለከተ እርስዎ በሚያስተዳድሩት በዚህ ክልል ያለውን ተጨባጭ እውነታ ቢነግሩን።**

**አቶ አሻድሊ:-** በአጠቃላይ በተለያዩ መስኮች (ዘርፎች) ከ34 ሺህ በላይ የሥራ እድል ተፈጥሮ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። ተጠቃሚዎችም ከራሳቸው አልፈው አካባቢዎቻቸውን ሁሉ መቀየር ችለዋል። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ብስክሌት እንኳን የማያውቁ አካባቢዎች ዛሬ ባለ መኪናዎች የሆኑት በክልሉ በተፈጠረው የሥራ እድል አማካኝነት ነው።

ከለውጡ በኋላ ለመስኖ ልማት ልዩ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን፣ በአጠቃላይ 11 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አሉ፤ ሰባቱ አነስተኛ ናቸው። በእነዚህ አማካኝነት በአመት እስከ ሶስት ጊዜ ማምረት የተጀመረ ሲሆን፣ ሽንኩርት፣ ድንች፣ በቆሎ እና ሌሎች ምርቶችም እየተመረቱ ይገኛሉ። አሁን ያለው ከተረጂነት ወደ አምራችነት የተሸጋገረ አርሶ አደር ነው። ይህን እያስፋፉ መሄድ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል። በእርግጠኛነት መናገር የሚቻለው የሰላም ችግሮቻችንን ሙሉ ለሙሉ ካስወገድን በጥቂት ዓመታት ውስጥ የፈለግነው የብልፅግና ምእራፍ ላይ እንደርሳለን። ራሳችንን ከመቻልም አልፈን ለሌላውም በመትረፍ ለሀገራችን ብልፅግና የበኩላችንን እንወጣ ለማለት እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡-ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ አሻድሊ፡-** እኔም እዚህ ድረስ በመምጣት ይህንን እድል ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ፋሽን

## የባህል አልባሳት ከበዓላት ባሻገር





**ሰሚራ በርሀ**

ዲዛይነር ገባይል አሰግድ ትባላለች:: የ‹‹ ገባይል ፎር ኦል›› ብራንድ መስራች ናት:: ‹‹ገባይል›› ማለት ሕዝባዊት፤ ለብዙ የሆነች የሚል ትርጓሜ እንዳለው ጠቅሳ፣ ‹‹ገባይል ለሁሉም›› የሚል ስያሜን ሰጥታ የባህል አልባሳትን ዲዛይን በማድረግ ታመርታለች:: በዚህም አልባሳቱን ለሁሉም አልያም ለብዙዎች ማድረስ የሚል እሳቤን ይዛ እየሠራች ትገኛለች::

ዲዛይነር ገባይል ሥራዎቿን ‹‹ቀለል ያለ ነገር ግን ውብ እና ግርማ ሞገስ የሚያላብስ ›› በማለት ትገልጻዋለች :: በሥራዎቿ የሀበሻ ልብስን እንደ ዋና ግብዓት ትጠቀማለች:: ‹‹ ለሀገር ባህል ልብስ በጣም ቅርብ ነኝ፤ ነገር ግን የሀበሻ ልብስ በበዓላት ብቻ ይለበሳል በሚለው ሃሳብ አልስማማም›› ትላለች::

በተለምዶ እነዚህ የባህል ልብሶች ሲሠሩ አንድን በዓል አልያም ሁነት ተመርኩዘው ነው:: ‹‹ገባይል ለሁሉም›› ግን የሀበሻ ልብስን ማንኛውም ሰው በፈለገው ቀን፣ የሥራ ቦታ ፣ መዝናኛ ላይ በነጻነት እንዲለብሰው አድርጋ በማዘጋጀት ለገበያ ታቀርባለች ::

ገባይል ትምህርቷን ያጠናቀቀችው በሜካኒካል ምህንድስና ቢሆንም፣ ከልጅነቷ አንስቶም ዲዛይነር የመሆን ፍላጎቷ እንደነበራት ትናገራለች:: የመጣሁበት ቤተሰብ ለፋሽን ቅርብ ነው የምትለው ዲዛይነሯ፣ እናቷ በቤት ውስጥ ሹራቦችን በመሥራት ፣ አያቷ እንዲሁ በቤታቸው ውስጥ ባላቸው መስፊያ ማሽን ለልጆቻቸው ልብሶችን ይሠሩ እንደነበር ትገልጻለች::

‹‹እናቴ ትምህርቴን እንዳልተው በማሰብ ፋሽን ትምህርት ቤት ገብቼ እንድማር አትፈቅድልኝም ነበር›› የምትለው ገባይል፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀችበት የናዝሬት ትምህርት ቤት የእጅ ሥራ ክፍለጊዜ የነበረው መሆኑ ገባይልን ይበልጥ ወደ ፋሽኑ እንድትሳብ እና ፋሽን ትምህርት ቤት ገብታ ለመማር ፍላጎት እንዲያድርባት አድርጓል::

ለፋሽን ያላት ፍላጎት ልጅ ሆና የሚገዙላትን አሻንጉሊቶች ልብስ እንድትቀይር፣ እያደገች ስትመጣ ደግሞ የራሷን ልብሶች እንደሚመቻቻት አድርጋ ዲዛይን እንድታደርግ ይገፋፋት እንደነበር ታስታውሳለች:: የአራተኛ ዓመት የሜካኒካል ምህንድስና ተማሪ ሳለች በታላቅ ወንድሟ አማካኝነት የመማር እድሉን አግኝታ ለአንድ ዓመት የፋሽን ዲዛይን ትምህርትን ተከታትላለች :: ይሄው ወንድሟ የልብስ መስፊያ ማሽን ገዝቶላት በቅርቧ ላሉ ሰዎች ልብሶችን መሥራት መጀመሯን ታብራራለች::

ገባይል ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ወደ ፋሽን ኢንዱስትሪው ሙሉ በሙሉ ትኩረቷን አደረገች :: በዚህም በሥራዎቿ ራሷን የምትገልጽበትን መንገድ ለመፈለግ ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም :: ሥራዎቿን ለማሳደግ በራሷ መንገድ እየተንቀሳቀሰች ባለችበት አፍሪካን ሞዛይክ የተሰኘ በየዓመቱ ለዲዛይነሮች የሚዘጋጅ ሥልጠና ላይ የመሳተፍ እድል አገኘች ::

ለአንድ ዓመት በቆየው ሥልጠና ማብቂያ ዲዛይነሮች የራሳቸውን ሃሳብና እይታ የሚገልጹበት ስብስብ ይዘው መቅረብ ይገባቸው ነበር:: ሥራዎቿ ለብዙዎች እንዲደርሱ ያደረገው ሁነት የተፈጠረውም በዚህ ሰዓት ነው ::

በዚህ ስብስብ ማስተላለፍ የፈለገችው ስለ አዕምሮ ጤና ነበር :: ‹‹ከዚህ ቀደም ስለ አዕምሮ ጤና ያለኝ አመለካከት ከመንፈሳዊ ነገር ጋር የተገናኘ ነበር፣ ነገር ግን በዙሪያዬ ድባቴ ውስጥ የገቡ ፣ በተለያየ ምክንያት ጭንቀት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የሚሉትን በጣም መስማት ጀመርኩ›› የምትለው ገባይል፣ በዚህ ሥራዋ አዕምሮም ልክ እንደሌላው የሰውነት ክፍላችን ይታመማል፤ ይታከማል በሚል ‹‹ከድባቴ ጀርባ ያሉ ውብ ልቦች›› በሚል የዲዛይን ሥራዎቿን ይዛ መቅረቧን ትናገራለች::

ይህ ስብስብ ገባይል አባቷን በሕይወት በማጣቷ ምክንያት በአንድ ወቅት የተፈጠረባት ድባቴ በሌሎች ላይ እንዳለ በማሰብ የአዕምሮ ጤና እክል ያጋጠመው ሰው አይድንም ወደ ቀድሞው አይመለስም ማለት ትክክል እንዳልሆነ እና ሰዎች በአዕምሮ ጤናቸው ምክንያት መፈረጅ የለባቸውም የሚል መልዕክትን ያስተላለፈ ነበር ስትልም ታብራራለች::

ሥራዎቿን በጀርመን በተዘጋጀ የበርሊን የፋሽን ሳምንት « ኒዮ የፋሽን መድረክ » ላይ አቀረበች:: መድረኩ በስፋት እውቅና እንድታገኝ አደረጋት፤ የአዕምሮ ጤናን በአልባሳት በኩል የገለጸችበት መንገድ በዓለምአቀፍ ደረጃ በሚታወቁት የበርሊንና እንግሊዝ ሀገር ጋዜጦች ላይም ለመውጣት ችላለች ::

ገባይል ሥራዎቿን ለማስተዋወቅ ማህበራዊ ገጾችን ትጠቀማለች:: የምትሠራውም በቤቷ ሆና ነው :: የፋሽን ዲዛይን መነሻዋ ከቤተሰብ እንደሆነ የምትገልጸው ገባይል፣ ‹‹እማዬ የወረደች ቀሚስ›› በሚል በአያቷ ስም የሠራችውን ስብስብ ለደንበኞቿ ማስተዋወቋንም ትናገራለች::

‹‹አያቴ በድሮው ጊዜ በተለያዩ ጌጣጌጦች የምታስጌጠው ልብስ ነበራት :: በጊዜው ጥሩ ኢኮኖሚ ላይ ያሉ ሴቶች በወርቅም ጭምር የተጌጡ ልብሶች ነበሯቸው::›› ስትል ጠቅሳ፣ ከዚህ በመነሳት በሸማኔ በተሠራው የፈትል ጨርቅ ላይ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ እንስቶች በአንገታቸው፣ በእጃቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ማጌጫዎች በማከል ልብሱ የተለየ ውበት እንዲሰጥ አድርጋ እንደምትሠራው ታብራራለች:: ጌጣጌጦቹን ከአክሱም ፣ ከላሊበላ እንደምታገኛቸው ተናግራ፣ ራሷ በምትፈልገው መንገድ ዲዛይን በማድረግ ጌጣጌጦቹን በልብሶቹ ላይ እንደምትጠቀምባቸው አመልክታለች::

የምትሠራው ልብስ በአብዛኛው የሰውነት ቅርጽን አይከተልም:: ወገብ ላይ እንደመቀነት የሚታሰሩ ጌጦች ስላሉት፣ እንስቶች ሲያሻቸው ለቀቅ ባለ መልኩ ቀለል ላለ ፕሮግራም እንዲሁም መቀነቱን አድርገው ደግሞ ለትልቅ ሁነት መጠቀም የሚችሉት ነው ::

እነዚህን አይነት ልብሶችን ገባይል ከአምስት ሺህ ብር ጀምሮ ለገበያ ታቀርባቸዋለች:: ‹‹በአብዛኛው የምንሠራው ለሴቶች ነው:: የወንዶች ግን በትእዛዝ ካልሆነ ገጥሞን አያውቅም›› ትላለች::

ልብሶቹን አይቶ የሚወዳቸው፣ ቀለል ያለ ልብስ መልበስ የሚፈልግ ሰው እንዳለ ሁሉ የሀበሻ ልብስ መሆኑን የሚጠራጠርም እንዳለ ትገለጻለች:: እኔ ግን ሥሰራው ራሴ የምወደውን ስለሆነ እንደኔ አይነት የልብስ ዲዛይን አማራጭ ላላቸው ሰዎች እሠራለሁ::›› በማለት ሥራዎቿን ትገልጻቸዋለች ::

ገባይል ምርቶቿን በተለያዩ ሰዎች መጠን ሰርታ በማዘጋጀት ሰዎች መጥተው የሚበቃቸውን ልብስ ለክተው ይዘው የሚሄዱበትን መንገድ መፍጠር ፣ ቅርንጫፎችን መክፈት እና ሥሯዎቿ ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲገኙ ማድረግ የወደፊት ህልሟ ነው :: በአሁኑ ወቅትም ሶስት ሠራተኞችን ይዛ እየሠራች ትገኛለች ::

# ትዝብት/ ማረፊያ

## አለባብሰው ቢያርሱ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

እነሆ ሰኔ ግም ብሏል፡፡ አይቀሬው ዝናብ ሊያመር፣ ጎርፍ ጭቃው ሊከተል ነው። ደመናው መጥቆር፣ ነጎድጓዱ ማስገምገም ጀምሯል፡፡ በሚያዝያና ግንቦት ሲመላለስ የከረመው ሙቀት አሁን ተንፈስ እያለ ነው፡፡ እውነት ለመናገር ክረምት ይሉት ጊዜ በራሱ ድንቅ ውበት አለው፡፡ ሁሌም ቢሆን ጭቃና ዝናቡን ፣ ብርድና ቆፈኑን በውዴታ ተቀብለን እናልፈዋለንና፡፡

ክረምት በተለይ ለእኛ ለአበሾቹ ብዙ ጉዳያችን ነው፡፡ ገጠር ካለው በረከት ባለፈ ተፈጥሯዊ ስጦታው ተናፋቂና ተወዳጅ ሆኖ በመስከረም ወር ይተካል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ የክረምቱን ገብቶ መውጣት በጥላቻ አናስታውስም፡፡ ‹‹እሰይ ጎሽ፣ ተገላገልን›› እያልን አናጥላላም፣አናማርርም፡፡ይልቁንም ለአንዳንዶቻችን ክረምት ሲገባ ጉዳያችን በእኩል ይታቀዳል፡፡ ዕቅዳችን በወግ ይከወናል፡፡

ክረምት በተለይ ጤናማ ሆኖ ከከረመ በትዝታ ታጅቦ ፣በነበር ታውሶ የሚያልፍ ነው፡፡ የክረምት በረከቶች ብዙ ናቸውና ወቅቱን በበጎ አስታውሶ ፣ ‹‹እንዲህ ነበር ›› ብሎ ማውጋቱ ብርቅ አይደለም፡፡ ጊዜው በደረሰ ጊዜ ከእሸት በቆሎው፣ከትኩስ ድንቹ፣ ከሚፋጀው የኩባያ ሻይ ጋር የሚኖር ቁርኝት ይበረታል፡፡እነዚህ ትንሽ የሚመስሉ፣ እንደአጋጣሚ የሚታዩ ሁነቶች ግን ሁሌም ቢሆን አብሮነትን ያሳምራሉ፡፡ ማህበራዊ አንድነትን ይጠብቃሉ፡፡ይህ እውነት ደግሞ የነባሩ ማንነታችን ማሳመሪያ ውበት ነው፡፡

ስለ ክረምቱ በጎነት ብዙ እያነሱ ማውጋት ይቻላል፡፡ ስላለፉትና ወደፊት ስለሚሆኑ በረከቶችም እንዲሁ፡፡ የዛሬው ትዝብቴ ግን በክረምቱ ጸጋ ላይ ብቻ የሚያተኩር አልሆነም፡፡ ከክረምቱ መግባት ጋር ተያይዞ እየሆኑ ያሉ እውነታዎችን ማንሳት ግድ ብሎኛል፡፡

ሰሞኑን በከተማችን አዲስ አበባ አንዳንድ የመንገድ ዳርቻዎች ተከማችተው የሚታዩ የቆሻሻ ክምሮች ለዓይን ይከብዳሉ፡፡ በተወሰነ ሜትር ርቀት ቁጭ ቁጭ ያሉት ቁልሎች ጠጋ ብለው ካዩዋቸው የማይቆጠሩት፣ የማይታዘቡት ጉድ የለም፡፡ ሁሉም በሚባል መልኩ በጭቃ አዋዜ ተለውሰዋል ፡፡

ጫማው፣ የላስቲክ ኮዳው፣ ፌስታል ላስቲኩ፣ ጨርቃጨርቁ፣አሮጌ ቁሳቁስና እርጥበት የማያሸንፋቸው ቁሶች ሁሉ በአይነትና በብዛት ይታያሉ፡፡እነዚህ እንደ መንገድ ገበያ ተዘርግተው የሚቆጠሩ ነውሮች በተአምር የመጡ አይደሉም፡፡ በአካባቢው የውሃ መውረጃ ቱቦዎች ላንቃ በብዙ ልፋት ተሰርስረው የወጡ እንጂ፡፡

እነዚህ ክምሮች በተለያዩ አጋጣሚዎች በአንዳንድ ሰዎች ግዴለሽነት የተወረወሩ ናቸው፡፡ ይህን አድራጊዎቹ እንደዋዛ የሚጥሏቸው ቁሶች ርቀው የሚሄዱ ባለመሆናቸው በቱቦዎቹ ሆድ ተከማችተው የመኖራቸው ጉዳይ ሁሌም ቢሆን ተለምዷል፡፡

በየመንገዱ የተሰሩት ቱቦዎች አስቀድመው መሠራታቸው ለተለየ ዓላማ ነበር፡፡ የውሃ መውረጃዎች ናቸውና ፍሳሽን በወጉ ያስተናግዳሉ፡፡ ስሪታቸው ደረቅ ቆሻሻንና የሚወገዱ ቁሶችን ለመቀበል አይደለም፡፡ በመንገድ ዳርቻ ላይ ውሃ እንዳይጠራቀምና መሄጃ እንዳያጣ በአግባቡ ተቀብለው ወደሚፈለገው አቅጣጫ የሚመሩ መስመሮች እንጂ፡፡

በተለምዶ የምናየው እውነታ ግን ከዚህ ዓላማ ፍጹም ተቃራኒ ሆኗል፡፡ እንዲህ እንደአሁኑ ክረምት በደረሰ ጊዜ የተጣሉትን ቅራቅንቦዎች እንደአገባባቸው መልሶ ለማውጣት የዋዛ አይሆንም፡፡ በቀላሉ ከቱቦው ደረት ተሰንቅረዋልና ቦታውን ጽዱ ለማድረግ ብዙ ስልትና ጉልበት ሊጠይቅ ግድ ይላል፡፡

አስቸጋሪውና አስደንጋጩ ጉዳይ ደግሞ ድንገቴው ዝናብ በመጣ ጊዜ የሚፈጠረው ችግር ነው፡፡ ከዝናብ በኋላ መንገዱ በጎርፍ ሲጥለቀለቅ፣ወሃው መሄጃ መድረሻ አጥቶ መራመጃ ሲጠፋ ማየት እየተለመደ ነው፡፡ይህ በዋዛ የሚታይ ውጤቱ ግን አደገኛ የሆነ አጋጣሚ ብዙዎችን ዋጋ እያስከፈለ ነው፡፡

ክረምት በገባ የመጀመሪያው ሳምንት በአንዳንድ አካባቢዎች ተሽከርካሪዎች በጎርፍ ተጥለቅልቀው ሲጨነቁ አይተናል፡፡ የገበያ ቦታዎችም በውሃ ተውጠው ዓይናቸው እያየ ሸቀጦቻቸው በጎርፍ መወሰዳቸውን እየሰማን ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ የተከሰተው ዝናብ ጎርፉ በቀላሉ ሄዶ የሚያበቃ አይሆንም፡፡ ከስፍራው ለቀናት ተኝቶ የሚከርመው ውሃ ተጨማሪ ኃይል እያከለ ሰፊ ባህር ሆኖ ይከርማል፡፡

ለዚህ ባህር መሰል ይዞታ ምክንያቱ የአካባቢው የውሃ መውረጃ ቱቦዎች በበርካታ ቁሶች መሞላታቸው ነው፡፡ ውሃውን ከቦታው አስወግዶ የተደፈኑ ቱቦዎችን ለማጽዳት ደግሞ ቀናትን መጠበቅ፣ፀሐይን መናፈቅ ግድ ይላል፡፡ አንዳንዴ በአንዳንድ ስፍራዎች ቦታውን በፍጥነት ለማጽዳት የውሃ መምጠጫ ፓምፖች ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ውሃው አረንጓዴ ምንጣፉን እንደለበሰ መስከረምን ይሻገራል፡፡

ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነቶቹ ክስተቶች ከዓላማ ያዘናጋሉ፡፡ ከስፍራ ያሰድዳሉ፡፡ለዚህ እንደማሳያ የቅዳሜና ዕሁድ የገበያ ቦታዎችን መፈናቀል መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዛሬ ላይ ለጀሞና አካባቢው ለዓመታት ሲያገለግል የቆየው የድንኳን ገበያ ወደሌላ ቦታ ለመሰደድ ተገዷል፡፡

ዛሬ የተለመደው ሰፊ መገበያያ ቦታ በስፍራው አይታይም፡፡ ክረምቱ ከመግባቱ አስቀድሞ መለስ ቀለስ ባለው ድንገቴ ዝናብ ሳቢያ ታሪኩ ተቀይሯል፡፡ አካባቢው በስፋት በጎርፍ መጥለቅለቁ የገበያውን ህልውና አላስቀጠለም፡፡ ገበያተኞችና ነጋዴው ስፍራውን ለቀው ወደሌላው ደረቅ ስፍራ ተሻግረዋል፡፡

በጣም የሚገርመው ጉዳይ ግን ዛሬም ገበያው በቆመበት ስፍራ የሚታየው የቆሻሻ አወጋገድ ነው፡፡ አሁንም ከገበያው የሚወገዱ አትክልቶች ፣ የሞቱ ዶሮዎች፣ ደረቅ ቁሶችና የማይበሰብሱ ዕቃዎች ወደ ቱቦዎች ይወረወራሉ፡፡ይህ ድርጊት ሲካሄድ የአካባቢው ደንብ አስከባሪዎችም ሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት አንዳች እርምጃ አይወስዱም፡፡ ሁሉንም በይሁንታ እያስተዋሉ ዝምታን አማራጭ አድርገዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመዲናችን አዲስአበባ መካሄድ በጀመረው የኮሪደር ልማት መልከ ብዙ ለወጦችን ማስተዋል ጀምረናል፡፡ይህ አዲስ እንቅስቃሴ ፈጣን የሥራ ባህልን ጨምሮ የከተማ ጽዳት ወሳኝነትን አስተምሮናል፡፡ ዛሬ ቀድሞ ቆሻሻ ይጣልባቸው የነበሩ ቦታዎች ወደ ድንቅ መናፈሻነት ተቀይረዋል፡፡

ከተማዋ እንደ ስያሜዋ አበባ ሆና እንድትኖር ጉልበቶች ኃይል ሆነው ለውጧን እያፋጠኑት ነው፡፡ የቆሻሻን ነውርነት በሚያሳይ መልኩ ጽዳት በወጉ ተተግብሮ ለዓይን ውበትና ለሀገር ዕድገት እየተሠራ ነው፡፡ይህ መልካም ጅማሬ ሀገራችን ይዛው የኖረችውን ክፉ ስያሜ የሚፍቅ ለሌሎች አቻ ከተሞች ጭምር ተምሳሌት የሚሆን ነው፡፡

ከዚሁ የከተማ ኮሪደር ልማት ጋር ተያይዞ በስፍራው የተቀመጡ የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራዎች በግልጽ ይስተዋላሉ፡፡ የእነሱ በስፍራው መቀመጥ ዋና ምክንያት ደግሞ ቆሻሻን በወጉ ለማስወገድና አብሮን የቆየውን ክፉ ባህል ለመቀየር ነው፡፡

ዛሬ ላይ የምናስተውለው ድርጊት ግን በተቃራኒው እየሆነ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ማስወገጃዎቹን በግልጽ እያስተዋሉት እንኳን በአግባቡ መጠቀምን አይሹም፡፡ እንደቀድሞው ልማዳቸው የእጃቸውን ሶፍትና ወረቀት የያዙትን የውሃ ፕላስቲክ ባሻቸው ቦታ ይወረውራሉ፡፡ እዚህ ላይ ችግሩ የአንድ ወገን ብቻ አይመስልም፡፡ይህን ክፍተት መጋራት ያለበት ቢኖር የሚመለከተው አካል ጭምር ይሆናል፡፡

መቼም ቢሆን ለሀገርና ማህበረሰብ ዕድገት የሚኖረውን ጉዳይ ተግብሮ ማሳየት የሚደነቅ ነው፡፡ ይህን ለውጥ ገሀድ ማድረጉ አንድ ነገር ሆኖ የተሰራበትን ዓላማና ሂደት ጭምር በሚገባ ማስገንዘብና ማሳወቅም ተገቢ ይሆናል፡፡

ይህ ሙከራ በአግባቡ የማይተገበር ከሆነ ደግሞ ለጥፋቱ ተመጣጣኝ ማስጠንቀቂያና ርምጃ በመወሰድ ጽዳትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብን መፍጠር የግድ ይላል፡፡ችግሮችን እንደዋዛ ማለፍ ግን ውሎ አድሮ ዋጋ የሚያስከፍለው ለሁሉም ነው፡፡ ይህ ችግር እንዳይደጋገም ደግሞ ኃላፊነቱ የሁላችንም ሊሆን ይገባል፡፡ ጉዳዩ ‹‹አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ›› እንዳይሆን ፡፡

# ዓለም አቀፍ



## በራፋ ስምንት የእስራኤል ወታደሮች መገደላቸውን ጦሩ አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የእስራኤል ጦር በደቡባዊ ጋዛ ባለችው የራፋ ከተማ ውስጥ እና ዙሪያ የሚያደርገውን ጥቃት እያጠናከረ ባለበት ወቅት ስምንት የእስራኤል ወታደሮች መገደላቸውን ጦሩ አስታውቋል።

ጦሩ እንደገለጸው፤ የተገደሉት ወታደሮች የኢንጂነሪንግ ቡድን አባላት መሆናቸውን እና በተሳፈሩበት ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ላይ ተጭኖ የነበረው ቁስ ሲመታ ፍንዳታ ተፈጥሮ ነው።

በምዕራብ ራፋ ቴል አል ሱልጣን የተፈጠረው ክስተት እየተመረመረ ነው ብሏል ጦሩ።

የፍልስጤሙ ታጣቂ ቡድን ሀማስ ወታራዊ ክንፍ ተሽከርካሪው የተጠመደ ፈንጅ ውስጥ መግባቱን እና ፍንዳታው መፈጠሩን ገልጿል።

የእስራኤል ታንኮች በቴል አል ሱልጣን እየገፉ እና ለበርካታ ጊዜ የተፈናቀሉ ፍልስጤማውያን የተጠለሉበትን ጠረፋማ ቦታዎች እየደበደቡ ናቸው።

ስምንት ወራትን ያስቆጠረው የእስራኤል-ሀማስ ጦርነት ወደ ተኩስ አቁም እንዲያመራ ዓለም አቀፍ ጫና ቢደረግም እስካሁን አልተሳካም።

በቀጠለው የእስራኤል ጥቃት በጋዛ ከተማ ዳርቻዎች ቢያንስ 15 ሰዎች መገደላቸውን እና ሌሎች ተጨማሪ አራት ሰዎች መቁሰላቸውን ሮይተርስ የጤና ባለሙያዎችን ጠቅሶ ዘግቧል።

እስራኤል ባለፈው ቅዳሜ እለት ጦሯ በግብጽ ድንበር በምትገኘው ራፋ በመሬት ላይ እና በሃማሴን በተሰሩ ቱቦዎች ውስጥ ተደብቀው የነበሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው የጦር መሳሪያዎች መያዙን አስታውቃለች።

ጦሩ የሀማስ ታጣቂዎች የሰብአዊ አገልግሎት ቀጣና ከሆነው የማዕከላዊ ጋዛ ክፍል አምስት ሮኬቶችን ባለፈው ሳምንት ዓርብ እንደተኮሱበትም ገልጿል።

ጦሩ ይህ ሀማስ የሰብአዊ አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ለመበዝበዝ እና ንጹሐንን እንደ ጋሻ ለመጠቀም ያለውን ሴራ የሚያሳይ ነው ሲል ከሷል።

የስምንቱ ወታደሮች ሞት የሀመል ፖለቲካ አራማጁ የቀድሞ ጀነራል ቤን ጋንዝ ስልጣን ከለቀቁ በኋላ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ ያጋጠማቸውን የፖለቲካ ቀውስ ያባብሳል ተብሏል።

ሀማስ በእስራኤል ላይ ጥቃት ከፍቶ 153 ሰዎች ካገተ እና 1200 የሚሆኑትን ከገደለ በኋላ እስራኤል እየወሰደች ባለው የአጸፋ እርምጃ የተገደሉ ፍልስጤማውያን ቁጥር ከ37 ሺህ ማለፉን የጋዛ ጤና ባለስልጣናት ይገልጻሉ።

## አንድ ግለሰብ የቻይናን ወታደራዊ ምስጢር የያዙ መጻሕፍት ከአንድ ዶላር ባነሰ ዋጋ መግዛታቸው ተነገረ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አንድ ግለሰብ የቻይናን ወታደራዊ ምስጢር የያዙ መጻሕፍት ከአንድ ዶላር ባነሰ ዋጋ መግዛታቸው ተነገረ።

ቻይና ውስጥ አንድ ግለሰብ በአካባቢው ከሚገኝ ቆሻሻ ማስወገጃ ወይም ሪሳይክል ሴንተር ከአንድ ዶላር ባነሰ ዋጋ የገዛቸው አራት መጻሕፍት የቻይናን ወታደራዊ ምስጢር የያዙ መሆናቸው አነጋጋሪ ሆኗል። መጻሕፍቱ ምስጢራዊ ወታደራዊ ሰነዶችን ይዘዋል ተብሏል።

የቻይና የብሔራዊ ደህንነት ሚኒስቴር በማህበራዊ ሚዲያ ባወጣው መግለጫ፤ ደውለው ያሳወቁትን ግለሰብ ባለፈው ሐሙስ እለት ማመስገኑን ኤፒ ዘግቧል።

በቤተሰብ ስማቸው ዛንግ እንደሚባሉ የገለጸው ሚኒስቴሩ፤ መጽሐፍቱ የያዙት ሰነድ ስለምን እንደሚያወሳ ግልጽ አላደረገም።

"ዛንግ የሀገሪቱን ወታደራዊ ምስጢር እንደገዙ አስበው መጽሐፍቱን ወደ ቤታቸው ወስደዋቸዋል" ያለው ሚኒስቴሩ ሌላ ዓላማ ባለው ሰው እጅ ገብተው ቢሆን ኖሮ ጉዳቱ ከፍተኛ ይሆን ነበር ሲል ገልጿል።

የሚኒስቴሩ መግለጫ ቢያንስ በሁለት ተወዳጅ የቻይና የዜና ድረ ገጾች ተለቆ ብዙዎች ተነጋግረውበታል። ለጉዳዩ የተሰጠው ሽፋን ብሔራዊ ደህንነት ከአሜሪካ ጋር ፍጥጫ ውስጥ ለገባችው ቻይና ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ግንዛቤ ለማስጨበጭ ዓላማ ያለው ነው ተብሏል።

ሚኒስቴሩ እንደገለጸው፤ መጻሕፍቱን የገዛው ግለሰብ የቀድሞ የመንግሥት ድርጅት ሠራተኛ ሲሆን፤ ወታራዊ ጋዜጦችን እና መጽሔቶችን መሰብሰብ የሚወድ ነው።

ግለሰቡ በቆሻሻ ማስወገጃው ጣቢያ ሁለት ሻንጣ ሙሉ አዳዲስ መጽሐፍትን ማግኘቱን እና ለአራቱ መጻሕፍት ስድስት ዩዋን መክፈሉን ሚኒስቴሩ አክሎ ገልጿል።

ሚኒስቴሩ እንዳለው ዛንግ ይህን ካሳወቁ በኋላ የደህንነት ሠራተኞች ወደ ጣቢያ በፍጥነት ሄደዋል። ምርመራ ከተደረገ በኋላ ሁለት ወታደራዊ ሠራተኞች መቅደድ ሲገባቸው 30 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ 200 መጻሕፍትን በ2.75 ዶላር ድጋሚ ጥቅም ላይ ለሚያውለው ማዕከል በመሸጥ ክስ ተመስርቶባቸዋል።

የደህንነት ሠራተኞቹ መጽሐፍቱን መያዛቸውን እና እንዲህ አይነት ሰነዶች የሚባክኑበት ክፍተት መዘጋቱንም ሚኒስቴሩ ጠቅሷል።


## የቅጥር ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት ከዚህ በታች በተገለጸው ክፍት የሥራ መደብ ላይ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾችን አወዳድሮ በቋሚነት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ ችሎታዎች | | የሥራ ልምድ/በዓመት | ደረጃ | ደመወዝ | ብዛት | የቤት አበል | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት አይነት | | | | | | |
| 1 | ሴክሬታሪ II | ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III ወይም 10+3 | የጽሕፈትና ቢሮ አስተዳደር ወይም ሴክሬታሪያል ሳይንስና አፊስ ማኔጅመንት ወይም ሴክሬታሪ ቴክኖሎጂ ወይም ኮምፒውተራይዝ ሴክሬታሪያል ሳይንስ እና አፊስ ማኔጅመንት ወይም ካስተመር ኮንታክት እና ሴክሬታሪያል ኦፕሬሽን ወይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም ኮምፒውተር ሳይንስ ወይም አይሲቲ ወይም አይቲ ወይም ኢንፎርሜሽን ሳይንስ ወይም ኢንፎርሜሽን ሲስተም ወይም አይቲ ሳፖርት ሰርቪስ ወይም ኮምፒውተር ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም ኢንፎርሜሽን ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ወይም አይሲቲ ሰፖርት ሰርቪስ ወይም አይሲቲ ሰፖርት እና ሲስተም ሰርቪስ ወይም አድሚንስትሬቲቭ ማኔጅመንት ቴክኖሎጂ ወይም አድሚንስትሬቲቭ ሰርቪስ ማኔጅመንት ወይም ቴክኖሎጂ ሲስተም እና አፊስ ማኔጅመንት ወይም አድሚንስትሬቲቭ አፊስ ማኔጅመንት ወይም ቴክኖሎጂ ሲስተም አፊስ አድሚንስትሬሽን ወይም አድሚንስትሬቲቭ ሰርቪስ ማኔጅመንት አድሚንስትሬሽን ኤንድ ኢንፎርሜሽን ሲስተም | 2 ዓመት በጽሕፈትና የቢሮ አስተዳደር ሥራዎች | 8 | 3,934.00 | 1 | 4000.00 | በዋናው መ/ቤት |

**ማሳሰቢያ፡-**

*በምዝገባ ወቅት አመልካቾች የትምህርት ማስረጃ ኦርጅናልና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

*በሌቭል የተመረቁ COC ምዘና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፣

*ከመንግስት ተቋማት ውጭ የተሰጡ የስራ ልምዶች የስራ ግብር የተከፈለባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፤

*ጾታ፣ አይለይም ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፣

*መመዝገቢያ ቀንና ሰዓት ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ባሉት 07 /ሰባት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ሆኖ ከሰኞ እስከ ሐሙስ ጠዋት 2፡30 - 6፡30 ሰዓትና ከሰዓት 7፡30-11፡30 እንዲሁም ዓርብ ጠዋት ከ2፡30 -5፡30 ከሰዓት 7፡30-11፡30 ሰዓት ድረስ ይሆናል፡፡

አድራሻ፡- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት ዋና መ/ቤት ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ፊት ለፊት በሚገኘው የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ በአካል በመቅረብ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት**

# ስፖርት





## ስፖርትን በጥናትና ምርምር መምራት ፈጣንና ዘላቂ ለሆነ ውጤት

**ብርሃን ፈይሳ**


ዓለም በቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ግኝቶች ተደግፋ በምትሽከረከርበት በዚህ ዘመን ልማዳዊ አሠራሮችና አካሄዶች ኋላ ቀርነትን እያስከትሉ ዋጋ ማስከፈላቸው እውን ነው። ይህ ሁኔታ በየትኛውም ዘርፍ ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ ስፖርትም ከወቅቱ ጋር መራመድ ካልቻለ ውጤታማነት የማይታሰብ ነው። ሳንሳዊ የስፖርት ጥናትና ምርምር ውጤቶች ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትና ስኬትን ለመጎናጸፍ ቁልፍ መሣሪያ በመሆናቸውም ዘመናዊው ዓለም ይህንኑ መንገድ በመከተል ላይ ይገኛል።

በልማዳዊ የስፖርት ሥልጠና እንዲሁም በስፖርተኞች የግል ጥረት ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ ስፖርትም በሳይንሳዊ አሠራር ተተክቶ ከጊዜው ጋር ራሱን ባለማሻሻሉ ከውጤታማነት እየራቀ መሆኑ እየታየ ነው። በመሆኑም የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎችና የጥናትና ምርምር ውጤቶች በጥቂቱም ቢሆን መነቃቃት ላይ ናቸው። በዚህ ረገድ ከሚሠሩ አካላት ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ሲሆን፤ ታዳጊ ስፖርተኞችን በዘመናዊ ሥልጠና ወደ ብቁ ስፖርተኝነት ከማሸጋገር ባለፈ የስፖርት ጥናትና ምርምር ማከናወን ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች መካከለ ይጠቀሳል።

በኢትዮጵያ በብቸኝበት በተደራጀ ሁኔታ አግልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘውና በርካታ የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎችን ያቀፈው አካዳሚው ዓመታዊ ሀገር አቀፍ የጥናትና ምርምር ጉባዔ ያዘጋጃል። ባለፉት ዓመታት 207 የሚሆኑ የጥናት ውጤቶችን ያሠራጨ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ በባለሙያና በቁሳቁስ (ቤተሙከራ) ይበልጥ ተደራጅቶ እየሠራ ይገኛል። ትኩረቱንም ሀገራዊ የስፖርት ችግሮችን የሚፈታ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ ማድረጉን በአካዳሚው የጥናትና ምርምር ማማከር ምክትል ዳይሬክተር አመንሲሳ ከበደ (ዶ/ር) ይናገራሉ። ይኸውም በአካዳሚው ብቻ ሳይሆን የምርምር ውጤቱን ሊጠቀሙበት የሚችሉ ስፖርታዊ ተቋማትን በማካተት፤ ጥልቀት ያላቸውና መፍትሄዎችን ማመላከት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ለአብነት ያህል ከሰሞኑ በተካሄደው የአካዳሚው 9ኛ የጥናትና ምርምር ጉባዔ ላይ ከቀረቡ ጉዳዮች መካከል አንዱ የ3 ሺህ ሜትር መሰናክል እና 5ሺ ሜትር ርቀት የሥልጠና ሞዴል ነው። አካዳሚው በሠልጣኞቹ ላይ ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ የሆነበትን መንገድ ከአትሌቶች አመላመል እስከ ምዘና ያለውን ሂደት ያካተተ ሞዴል ይፋ አድርጓል። ይኸውም በሀገር አቀፍ ደረጃ የአትሌቲክስ ስፖርትን በእጅጉ ሊጠቅምና ለስኬታማነትም ጉልህ ድርሻን ሊያበረክት እንደሚችል ታምኖበታል። ሌላኛው በመድረኩ ላይ የቀረበው ለኢትዮጵያ ስፖርት በእጅጉ ስጋት የሆነው የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ጉዳይን የሚመለከት ጥናት ሲሆን፤ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲሁም አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በመሆን የተሠራ ነው። በሀገሪቷ ያለውን ተጠቃሚነት በግልጽ ከማመላከት ባለፈ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚጠቁም ጥልቅ የምርምር ውጤት በመሆኑ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልም ነው።

አካዳሚው በራሱ አቅምና ሌሎች ባለሙያዎች ከሚሠሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ባለፈ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሠሩ ጥናቶችን ማሰራጨት አንዱ እንደመሆኑ ሀገር አቀፍ የስፖርት ጆርናልን ሥራ ላይ ማዋሉ ይታወቃል። ጆርናሉ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘና የአህጉር አቀፍ መሰል ተቋማት ጋር የሚሠራ በመሆኑም ምሁራኑ ጥናቶቻቸውን የሚያሳትሙበትን




**አካዳሚው ትኩረቱን ሀገራዊ የስፖርት ችግሮችን የሚፈታ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ አድርጓል፤**

እድል ማመቻቸት ችሏል። በጉባዔው ላይ ተሳታፊ ከሆኑ አካላት መካከል 9 የሚሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጥናቶቻቸውን ማቅረባቸውም ተደራሽነቱን ከማስፋት አንጻር የሚኖረው አስተዋጽኦ ቀላል የማይባል መሆኑንም ምክትል ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ።

ይሁንና በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥናታዊ ውጤቶችን ወደ ተግባር ከመቀየር አንጻር ሰፊ ክፍተት አለ። በስፖርቱም ችግር ፈቺ ሊባሉ የሚችሉ ጥናቶችን መሬት ማድረስ አለመቻሉ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል። ለክፍተቱ በምክንያትነት ጥናቶቹ በቀጥታ ተጠቃሚው ጋር አለመድረሳቸው እንዲሁም የመሠረተ ልማት ችግር መኖሩ ከጉባዔው ተሳታፊዎችም ጭምር አስተያየት ተሰጥቶበታል። ምክትል ዳይሬክተሩም ለዚህ ከሚያነሷቸው ሃሳቦች መካከል አንዱ ጥናቶች ሲሠሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘቡ እንዲሁም ሥራ ላይ በሚውሉበት ቋንቋና ሁኔታ ያልተዘጋጁ መሆናቸውን ነው። በሌላ በኩል እንደዘርፍ ጥናቱ የሚያመጣው ለውጥ ስጋት የሚሆንባቸው አካላት መኖራቸው ቁርጠኛ አፈጻጸም አስፈላጊ ነው።

የስፖርት ኢንዱስትሪው ለምርምርና ቴክኖሎጂ በሩን መዝጋቱ ዋጋ የሚያስከፍልም ነው። ክለቦች ለአንድ ስፖርተኛ ከፍተኛ ገንዘብ ከማውጣት ይልቅ ለቴክኖሎጂ፣ ለታዳጊዎች ልማት፣ … ትኩረት መስጠት ቢቻል ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ውጤት ሊመጣ እንደሚችልም ምክትል ዳይሬክተሩ ያስገነዝባሉ።

## Beeksiisaa Qaxarta

Dhaabbatni Bosonaa fi Bineensaa Bosona Oromiyaa gita hojii Ogeesaa IT fi Data Beezii irratti dorgomsiisee Dhaabbidhaan qaxaruu Barbaadaa. Kanaafuu Ogeessotni ulaagaa gitchi gaafatuu guuttaan guyya beeksisnii kun bahee irraa eegalee guyya hojii 5(shan) keessatti ragaa barnootaa Orjinaalaa fi kooppii hin deebiinee qabachuun Dareek tooreettii Bulchiinsaa Qabeenyaa Namaa fi Ijaarsaa Dandeetti Biiroo lakk. 206 tti argamuun galmaa'uu kan dandeessan ta'uu ni beeksifna.

| Waamama gita hojii | Gosaa barumsaa fi muxannoo hojii | Baayina | Sad | Mindaa | Iddoo Hojii | Haalaa Qaxaraa |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **Ogeesaa IT fi Data Beezii** | **Digirii jahlabaa fi isaa ol, Informeeshin Teeknolojii , Kompiitar Sayinsii, ICT fi kan walfakaatan muxanno hojii Waggaa 5(Shan)** | **01** | **G-15** | **15,255.00** | **Waajjiraa O1'aanaa** | **Dhaabbiidhaan** |

Hub. Teessoon keenyaa Qabanaa Bataskaanaa Madanialam Cinaa

Odeeffannoo dabalataaf : Iakk.Bilbilaa 011-124-03-18

**Dhaabbata Bosonaa fi Bineensaa Bosona Oromiyaa**

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

የጎተራ ኮንዶሚኒየም የጋራ መኖሪያ የህብረት ስራ ማህበር የልጆች መጫወቻ (ዥዋዥዌ ባለ 3 ብዛት 17፤ሸርተቴ ብዛት 13፤እሽክርክሮሽ 12 ሰው የሚይዝ ብዛት 3 ዥዋዥዌ ባለ 8 ብዛት 3) በጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል። በዘርፉ ህጋዊ ፈቃድ ያላችሁ ማናችሁም ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ጀምሮ የማይመለስ ብር 300 በመክፈል ማህበሩ ጽ/ቤት በመምጣት ስለ ጨረታ ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ሰነድ ወስዳችሁ እንድትጫረቱ ሆኖ በሰባተኛው ቀን ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት በታሸገ ፖስታ በማስገባት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሶስት ሰዓት ተኩል ይከፈታል ማንኛውም ተጫራች የጨረታ "ማስከበሪያ(Bid bond) የሚያቀርበውን ጠቅላላ ዋጋ በመቶ(2%)CPO ከታወቀ ባንክ በማኅበሩ ስም ማስያዝ አለበት።

ማህበሩ የተሻለ አማራጭ(መንገድ) ካገኘ በጨረታው አይገደድም።

ለተጨማሪ መረጃ ስልክ ቁጥር 0114702254 / 0114701247

**የጎተራ ኮንዶሚኒየም የጋራ መኖሪያ**

**የህብረት ስራ ማህበር**

## ማስታወቂያ

በተስፋዬ ልዑል በ05/10/2016 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የሠሌዳ ቁጥር ሥከ-GR-0013 የሆነ ግሬደር፣ የሠሌዳ ቁጥር ሥከ-EX-0029 የሆነ ኤክስካቫተር ፣ የሠሌዳ ቁጥር ሥኩ DZ-0351 የሆነ ዶዘር፣ የሠሌዳ ቁጥር ሥከ-LD-0048 የሆነ ሎደር እና የሠሌዳ ቁጥር ሥከ-GR-0295 የሆነ ግሬደር የሆኑ ማሽኖች የብረት ሰሌዳ የጠፉባቸው መሆኑን ገልፀው ምትክ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በዚህ መሰረት ሰሌዳውን ወድቆ ወይም ተሰርቆ ያገኘ ወይም በሌላ ሁኔታ ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር እንዲያመለክቱ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የትራንስፖርትና ሉጀስቲክ**

**ሚኒስቴር**